ክፍል ሦስት

የቤተ ክርስቲያን ሕይወት

ቤተ ክርስቲያን ምን እንደሆነችና ምን ይዘት እንዳላት አስቀድመን እንገልጻለን።

ቤተ ክርስቲያን ንስሐ በመግባት የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ለእነርሱ መዳን መሆኑን በማመን ከዓለም ርኵሰትና ከሰይጣን ግዛት ተጠርተው ለእግዚአብሔር የተለዩ ምእመናን ስብስብ ነች። እነዚህ ምእመናን በአንድ ላይ ተሰብስበውም ሆነ በዓለም ዙሪያ ተበትነው ቤተ ክርስቲያን ተብለው ይጠራሉ። (1ኛ ጴጥ. 2፡9፤ የሐዋ. 2፡41-47፤ የሐዋ. 5፡11፤ 11፡26፤ 13፡1፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡18፤ 14፡19፥ 28፥ 35፤ 16፡19፤ ሮሜ 10፡8-9፤ 16፥ 4፥ 5፥ 23፤ ገላ. 1፡2፤ ተሰ. 2፡14፤ ቆላ. 1፡18፡24፤ 4፡15፤ ፊልሞና 2፤ ኤፌ. 1፡22፤ 3፡10፥ 21፤ ማቴ. 18፡20) ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን የቁዱስን ጉባኤ ናት (1ኛ ቆሮ. 1፡2)።

ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ አካል፥ በመንፈስ ቅዱስ መቅደስ ወይም ማደሪያ፥ በሕንጻ፥ በሙሽራይት፥ በላይኛይቱ ወይም በሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም በእውነት መሠረትና አምድ ተመሰላለች (1ኛ ቆሮ. 12፡12-27፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 2፡20-21፤ ቆላ. 1፡18፤ 1ኛ ቆሮ. 3፡16፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡2፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡5፤ ገላ. 4፡26፤ ዕብ. 12፡22፤ ራዕ. 19፡27፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡15)

ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት፤ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታንም የተላበሰች ነች። አግባብና ሥርዓት እንዲኖራት ልዩ ልዩ መሪዎች ተሰጥተዋታል (ኤፌ. 2፡20-22፤ 4፡4-11፤ ሮሜ 12፡3-8፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡4-11፤ 14፡29-40) ቤተ ክርስቲያን የማሰርና የመፍታት ሥልጣን አላት (ኤፌ. 4፡11-13፤ ማቴ. 18፡18፤ ሉቃስ 10፡18-19፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡3-5፥ 12፤ 6፡1-5)።

1. የቤተ ክርስቲያን አባል የመሆን ጠቃሚነት

የቤተ ክርስቲያን አባል ሲባል የእግዚአብሔር ቤተሰብነትን፥ በአንድ ክርስቶስ አካል አብረው ያሉትን፤ ያመለክታል፥ (ኤፌ. 2፡19፥ 3፡6፤ 4፡4፥ 25)።

እንግዲህ በጌታ ኢየሱስ ያመነና የተጠመቀ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅነትን ስለአገኘ ከእርሱ ቀድመው የእግዚአብሔር ቤተሰብ ከሆኑት

የእግዚአብሔር ልጆች ጋር በአንድነት መኖር የሚያስፈልገው ነው። ይህ ልክ በአንድ ቤተሰብ ሌላ ልጅ በተወለደ ቁጥር የዚያ ቤተሰብ አባል መሆኑ ያለ ያህል ነው። እንዲሁም በጌታ ኢየሱስ ካመንህና ከተጠመቅህ፥ በሐዋርያት ሥራ ይህንኑ ያደረጉት ከሌሎች ምእመናን ጋር እንደተደባለቁና እንደኖሩ አንተም በቤተ ክርስቲያን በሚደረገው ኅብረት ሁሉ በጸሎት፥ የጌታን እራት በመውሰድ ወንጌልን በመመስከርና በመሳሰሉት መካፈል ይኖርብሃል።

አንድ የሰውነት ክፍል በሌሎቹ ብልቶች አልተደሰትሁምና ተቆርጬ ልቀመጥ ልትል እንደማትችል ሁሉ አንተም በቤተ ክርስቲያን ካሉ አባላት ወይም አገልጋዮች ጋር አልተጣጣምሁም ብለህ ራስህን ከኅብረቱ ማግለል አንድ የከሰል ፍም ከሌሎች ፍም ከሰሎች ቢለይ ፍምነቱ እንደሚቀር አንተም በመንፈሳዊ ሕይወትህ እንድትቀዘቅዝና በሰይጣን ወጥመድ እንድትወድቅ ያደርግሃል።

«ብረት ብረትን እንደሚስል ሰውም ባልንጀራውን ይስላል» የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስን ምክር ስማ። (ምሳ. 27፡17) «ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድትነቃቃ ከሌሎች ምእመናን ጋር ተያይ፥ መሰብሰብህንም አትተው እንዳውም ኅብረትህን አጠንክር» (ዕብ. 10፡24-25)።

ምንም እንኳ ስፍራህን ሊያስለቅቁ ብዙ የሥጋና የዲያብሎስ ውጊያዎች ቢነሱብህም «በለሱን የጠበቀ ፍሬውን ይበላል፥ ጌታውንም የሚጠብቅ ይከብራል» በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት በጌታ ሕዝብ መካከል በአባልነትህ ፀንተህ ብትኖር ጌታ በዚያው በአዘንህበት ስፍራ ታላቅ በረከትና ደስታውን እደሚያፈስልህ እመን፥ ጌታ በነገር ሁሉ ይርዳህ (ዘፍጥ. 26፡1-6፥ 12-14)።

2. የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን መቅሰም በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ይረዳል

ንስሐ ገብተህ ጌታ ኢየሱስን እንደግል አዳኝህ ካመንህበት ጊዜ ጀምሮ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሆነሃልና ለዚህ አዲስ በመንፈስ ለተወለደው ሕይወትህ መንፈሳዊ ምግብ በየዕለቱ መመገብ ያስፈልግሃል። ለእስራኤል ልጆች በሲና ምድረ በዳ እግዚአብሔር መናን በአዘነበላቸው ጊዜ የታዘዙት ትእዛዝ በስድስተኛው ቀን ለሰንበት ጭምር እጥፍ ከመልቀም በስተቀር፥ በየዕለቱ ወጥተው የሚበቃቸውን ያህል መልቀም ነበር፤ ይህንንም ደግሞ በየቀኑ ለ40 ዓመታት አደረጉት። ከዚህ ታላቅ ትምህርት ልትወስድ ትችላለህ፤ እግዚአብሔር

ከምድር ዓለት ውኃን እንዳፈለቀላቸው፥ ከምድር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ በተአምር አስገኝቶ ምግብ መስጠት ይችል ነበር፤ ግን ይህን አላደረገም። ምክንያቱ ምን ይሆን? መልሱን በዘዳግም መጽሐፍ ላይ እናነባለን። ሰውም «ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ነገር ሁሉ በሕይወት እንዲኖር እንጂ ሰው በእንጀራ ብቻ በሕይወት እንዳይኖር ያስተወቅህ ዘንድ አስጨነቀህ፤ አስራበህም አንተም ያላወቅኸውን አባቶችህም ያላወቁትን መና በላህ» ይላል (ዘዳ. 8፡1-3)።

ከሰማይ የወረደው መና የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን ጌታ ኢየሱስን የሰማይን እንጀራ ነው፤ ያም ሰማያዊ እንጀራ ለዓለምና ለአንተም ሕይወትን የሚሰጥ ነው (ዮሐ. 6፡32-35)። ስለሆነም በሕይወት ለመኖር በየቀኑ በእግዚአብሔር ቃል ተሞላ፤ ቃሉ በዚህ ዓለም ለምትኖረው ኑሮ ዕለታዊ መብራትና ብርሃን ነው፤ የምትሄድበትን መንገድ የሚመራህና፥ የሚያስተምርህና ከኃጢአትም አንተን ለመጠበቅ መከላከያህ ነው፤ እንዲሁም በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት በሕይወትህ ለመቆም ይረዳሃል፤ የክፉውንም ፈተና ለመቋቋም ማጥቂያ ሰይፍህ ነውና አንሣውና ተጠቀምበት።

ስለሆነም በየዕለቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በተከታታይ ብታነብና ብታሰላስለው፤ የሚናገርህንም ብታደርገው በውኃ ዳር እንደተተከልች ፍሬዋንም በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ትሆናለህ፤ የምትሠራው ሁሉ ይከናወንልሃል። የተሳካም ኑሮ ትኖራለህ። በኃጢአት እንኳ ብትወድቅ ቃሉን ስታነብና ስትታዘዝ አንጽቶ ይቀድስሃል። ከዚህ በተጨማሪ በሰንበት ትምህርት ቤትም ሆነ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተህ ለመማር መንፈሳዊ መጻሕፍትንም በማንበብ ብትተጋ፥ ለራስህ ተጠቅመህ ለሌሎችም ወገኖችም ትተርፋለህና ወንድሜ ሆይ! እግዚአብሔር የሚናገርህ በቃሉና በመንፈሱ ነውና በዚህ ጉዳይ ትጋትን እንድታሳይ እመክርሃለሁ።

እዚህ ላይ አንዲት እንግሊዛዊት እናት ለሌሎች ዘመዶቹ ልዩ ልዩ ንብረትን ስታወርስ በጣም ለምትወደው ልጇ ግን «ለልጄ ይህን መጽሐፍ አውርሻለሁ» ብላ መጽሐፍ ቅዱስን ሰጠችው ይባላል፤ ልጁ ከእናቱ የተሰጠውን መጽሐፍ ቅዱስ ንቆ ሳይገልጠውና ሳያነበው ብዙ ዘመን ያሳልፍና አንድ ቀን ገልጦ ማንበብ ሲጀምር፥ በየገጹ መጽሐፍ ቅዱስን ቢያነብ ኖሮ ያገኝ የነበረውን የእንግሊዝ ፓውንዶች ያገኛል፤ ግን ከጊዜአቸው ማለፍ የተነሣ ፓውንዶቹ ተለውጠው የገንዘብ ዋጋቸውን አጥተው ያገኝና በጣም ያዝናል፤ ወንድሜ ሆይ! በመጽሐፍ ቅዱስ የተፃፉት ቃላት ብዙ ዋጋ ያላቸው በዘመናት ውስጥ ዋጋቸውን

የማይቀንሱ፥ ለሕይወትህ የሚጠቅሙ ናቸውና የዚያ ልጅ ምሳሌ እንዳይደርስብህ ቸል አትበላቸው።

3. የግል፥ የቤተሰብና የሰፈር ጸሎትን ማዘውተር መንፈሳዊ ጥንካሬን ይሰጣል

ስለ ጸሎት የተባሉ ጥቅሶች ተዘውትረው በአንዳንድ ሰዎች ቤት ይነበባሉ፥ ለምሳሌ «ዓለምን ከማየትህ በፊት እግዚአብሔርን እይ»፥ «ጸሎት ሁሉን ነገር ይለውጣል»፥ «አብረው የሚጸልዩ ቤተሰቦች አብረው ይኖራሉ»፤ «ጸሎት የነፍስ እስትንፋስ ነች» የሚሉትና የመሳሰሉት፤ እነዚህ ታዲያ የጸሎትን ጥቅም ከተለማመዱ ወገኖች ሕይወት ተጨምቀው የወጡ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከእነዚህ በላይ ስለ ጸሎት ጠቃሚነትና አስፈላጊነት የሚናገረው አለ።

«አንተ ግን ስትጸልይ፥ ወደ እልፍኝህ ግባ፥ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፥ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል...

ለምኑ ይሰጣችሁማል፥ ፈልጉ ታገኙማላችሁ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል።

የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልግም ያገኛል፥ መዝጊያውንም ለሚያንኳኳው ይከፈትለታል።

በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን አይሰጣቸውም... እግዚአብሔር እንኪያስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ለሚታገሳቸውም ምርጦች አይፈርድላቸውምን? እላችኋለሁ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል።

... ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉ ጸልዩም መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው።

... በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤ ሁልጊዜ ስለሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንና አባታችንን ስለሁሉ አመስግኑ...

... ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፥ ሳታቋርጡ ጸልዩ፥ በሁሉ አመስግኑ፥ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና...

በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምሥጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ። አእምሮንም

የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።

ከማመስገን ጋር በጸሎት እየነቃችሁ ለእርሱ ትጉ፤ በዚያን ጊዜም ስለ እርሱ ደግሞ የታሰርሁበትን የክርስቶስን ምስጢር እንድንናገር እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ ልናገር እንደሚገባኝ ያህል እገልጠው ዘንድ ጸልዩልኝ...

ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ ለእርሱ እናቅርብለት

... በመንፈስ ቅዱስም ኃይል ጸልዩ፤ የፃድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።

... ለሰዎች ኃጢአታችሁን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና።

እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ፀጥና ዝግ ብለን እንድንኖር ልመናና ጸሎት ምልጃም ምሥጋናም ስለሰዎች ሁሉ በተለይም ለነገሥታትና ስለ መኳንንት ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።

... ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል። በዚያን ጊዜም ይጠግሉ።

... ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም።

እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል።

ደግሞ እላችኋለሁ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ። ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።

ሃሌሉያ። እግዚአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት፤ በኃይሉ ጠፈር አመስግኑት፤ በችሎቱ አመስግኑት፤ በታላቅነቱ ብዛት አመስግኑት፤ ... እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን። ሃሌሉያ። እያለ ስለ ጸሎት ያሳስባል።

ከዚህ በላይ እንዳነበብኸው ጸሎት ሕብረትን ውዳሴንም ምስጋናንም፥ ስግደትን፥ ልመናን፥ ምልጃን፥ ያጠቃልላል። ጸሎት ደግሞ ለግል፥ ለቤተሰብ፥ ከምእመናን ጋር በሰፈርና በቤተ ክርስቲያን

በመጸለይና በመጾም ለሕይወት ብርታትና ጠላት ዲያብሎስን ለማሰር፥ ለመቃወም፥ ለማስወጣት፥ ከእግዚአብሔር ዋጋ ለማግኘት፥ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት፥ ፍርድንና ሰላምን፥ የኃጢአት ይቅርታን ለማግኘት፥ ለሰው ሁሉና በተለይም በሥልጣን ላይ ያሉ ሁሉ ወንጌል እንዲሰበክ፣ ፀጥታን ሰላምን እንዲያስከብሩ፤ ትዳር እንዲሳካና ለመሳሰለው እጅግ ጠቃሚነት አለው። ይህን ከተገነዘብህ በእግዚአብሔር በመታመን፥ በኢየሱስ ስም በመጠቀም፥ ንስሐ በመግባት፥ ይቅር ባይ በመሆን፥ ባለመሰልቸት፥ በነገር ሁሉ፥ በማናቸውም ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በግልህ የጥሞና ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ይኑርህ። በቤተሰብና በሰፈርም ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት አድርገህ ከምስጋና ጋር ያለማቋረጥ ጸልይ። በያዕ. 5፡16 እንደተጻፈው «የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች» ይላል። የሰላምም አምላክ በረከቱንና ሕይወቱን፥ ምህረትና ቸርነቱን የሰማዩንም ጠል ያፈስልሃል። አንተም ብርቱ ክርስቲያን ትሆናለህ፥ በመታዘዝህም በመንፈስ ሙላትም ባለማቋረጥ ትኖራለህ።

4. ስጦታን አውቆ ማገልገል ለአማኝ ወሳኝ ነው

አንድ ሰው ጌታ ኢየሱስን ካመነበት ጊዜ ጀምሮ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ይቀበላል። መንፈስ ቅዱስም ለአማኙ ለብቻው እያካፈለ ስጦታን ይሰጣል። ስጦታም የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስን ለመግለጥ ለጋራ ጥቅም ሲሆን በስጦታውም በቤተ ክርስቲያን ያሉትን ምእመናን ለማነጽና ከወንጌል ውጭ ያሉትን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲመልስ ነው፤ ከዚህም በስተቀር ምእመን፥ በአገልግሎቱ፥ ለሞተለትና ለተነሣለት ጌታ ኢየሱስ ለመኖርና እግዚአብሔርን ለማክበር ዓላማ ሊኖረው ይገባል።

በስጦታህ ለማገልገል የሚከተለውን እርምጃዎች ውሰድ

- ስጦታህን መንፈስ ቅዱስ እንዲገልጽልህ ጸልይ።
- ስለመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አጠቃቀም ከቃሉ ጋር በማመሳከር በመንፈሳውያን ሰዎች የተጻፉትን ገንቢ መጻሕፍትን አንብብ።
- ዝም ብለህ በቤተ ክርስቲያን ቁጭ ከማለት እግዚአብሔር በሰጠህ ችሎታ ሌሎችን ለማገልገል ጥረት አድርግ።
- ከአንተ በፊት በአገልግሎት የቀደሙትን ምሳሌ አድርገህ አገልግል፤ ሆኖም ለማስመሰል አትሞክር።

- እግዚአብሔር በሽማግሌዎችና በሌሎችም አገልጋዮች ሊገልጥልህ ስለሚችል የእነርሱን ጸሎትና ምክር ጠይቅ። እነርሱም የሚሰጡህን አገልግሎት ዝቅተኛ ነው ሳትል ለእግዚአብሔር እንደምታደርገው በመቁጠር አገልግል።

- የተሰጠህን አገልግሎት ካልቀበርህና በዚያች ታማኝ ከሆንህ ከጊዜ በኋላ እግዚአብሔር ስጦታህን ያሳድጋል፥ ያበዛውማል። እርሱ «በጥቂቱ የታመነውን በብዙ እሾመዋለሁ» ብሏልና።

ከዚህ በላይ የተጻፈውን ለማጠናከር ስለ አገልግሎት በመጠኑም ቢሆን ከመጽሐፈ ነህምያ አንዳንድ አሳቦችን ብታውቅ ይጠቅምሃልና እንግለጽልህ።

- እግዚአብሔር ለአገልግሎት አደራ የሚጥልበት ሰው ሸክም የሚሰማውን ነው። ለአገልግሎት ሸክም ካለህ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራህ ጸልይ (ምዕ. 1)።

- እግዚአብሔር በሚመራህ አገልግሎት ክንዋኔ እንደሚሰጥህ በፍጹም ልብህ በመታመን «የሰማይ አምላክ ያከናውንልኛል እኔም ተነሥቼ አገለግላለሁ» ብለህ ተሰማራ (ምዕ. 2)

- የአገልግሎትህን ዓይነትና ድርሻህን እወቅና ከሌሎች ጋር በጎብረት ሥራ (ምዕ. 3)።

- አገልግሎትህን ስትፈጽም ሰይጣን ተቃዋሚዎችን ሊያስነሣ እንደሚችል አውቀህ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ተቋወመው (ምዕ. 4)።

- በአገልግሎት ሌሎች ሲቀዘቅዙ አይተህ አገልግሎትህን ቸል እንዳትል እግዚአብሔርን ፍራና በቅድስና ተመላለስ (ምዕ. 5)።

- ክፉ ወሬ በማስወራት፥ በማስፈራራትና በአስመሳይ–አገልጋዮች በመጠቀም ሰይጣን ችግሮችን ሊያስነሣ ውጊያው ከእርሱ መሆኑን አውቀህ በእግዚአብሔር ኃይል ተቋቋመውና አገልግሎትህን ፈጽም (ምዕ. 6)።

- በቤተ ክርስቲያን ኃጢአትን እያየህ ዝም አትበል፤ ኃጢአት ተራብቶ አገልግሎት እንዲቆም ያደርጋልና (ምዕ. 7)።

- ሁሉን እኔ ላድርግ አትበል፥ ሌሎችን በአገልግሎትህ ወክል፤ ለእግዚአብሔር ቃል ስፍራ ስጥ (ምዕ. 8)።

- በየጊዜው በእግዚአብሔር ፊት ስለ አገልግሎትህ ቃል ኪዳን ግባ (ምዕ. 9–11)።
- እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን የሚያደርገውን እያየህ በጌታ ደስ ይበልህ (ምዕ. 12)
- ሰይጣን ሃይማኖታዊ ሰዎችን በመጠቀም ከዚህ በፊት የተስተካከለውን ሊያበላሽ ይችላልና ያንን ከማስተካከል ተስፋ ቆርጠህ ዝም አትበል (ምዕ. 13)።

ሰዎችን በማገልገል የሚገጥሙ ፈተናዎችን አውቆ ስለ መከላከል

ዶክተሮች አንዳንድ በሽታዎች በሥራ ምክንያት እንደሚመጡ ይናገራሉ። እንደዚሁም ሰዎችን የሚያገለግል ሰው እንደሌሎች ሰዎች ከወደቀው የሰው ዘር የተገኘ በመሆኑ ከአገልግሎቱ አንፃር የሚከተሉት ዓይነት ፈተናዎች ሊያጋጥሙት ስለሚችሉ ምን እንደሆኑ አውቀህ ራስህን ከእነዚህ ወጥመዶች ጠብቅ።

- አብዝተህ ስለ አንድ ሰው ጉዳይ ለማወቅ መፈለግ።

ይህ ፈተና አንድ አገልጋይ የሚረዳውን ሰው መርዳት ጥሎ ስለዚያ ግለሰብ የግል ጉዳይ ጠልቆ ለማወቅና ይህን ፍላጎቱን ለማርካት ብዙ መረጃ ከግለሰቡ እየጠየቀ ለመረዳት የሚያደርገው ጥረት ነው። አገልጋይ ይህን የሚያደርግበት ዋናው ምክንያት ያ የራሱም ችግር ስለሆነ ደካማ ጎኑን ለማርካት ከሚያደርገው ጥረት የተነሣ ነው። ይህ ደግሞ የሰውየውን ብዙ ግላዊ ምሥጢር ሁሉ የሚነካ ነውና በእርሱ ኪሣራ የራስህን ጥቅም አትሻ። ስለዚህ ስለደካማ ጎንህ እወቅና የዚህ ዓይነት ፈተና ሲገጥምህ ለማሸነፍ እንድትችል የመንፈስ ቅዱስን ርዳታ ጠይቅ።

- በተቃራኒ ጾታ መፈተን

አገልጋይ በያዘው አገልግሎት፥ በሥልጠናው እና በልምዱ ምክንያት ተቃራኒውን ጾታ የመርዳት እድል ይገጥመዋል።

በዚህ ጊዜ አገልጋዩም ሆነ ተመካሪው ተቃራኒ ጾታ ሳያውቁት የሥጋ ፍትወት ስሜታቸው ሊቀሰቀስ ይችላል፤ ስለሆነም ይህ ሊያጋጥም እንደሚችል አስቀድሞ አውቀህ ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ከመነጋገርህ በፊት መንፈስ ቅዱስ እንዲቆጣጠርህ ራስህን

ማስረከብ አለብህ። ማቴ. 26:41 እኔ በዚህ አልፈተንም በማለት የምትመካ ከሆነ «ቆሜአለሁ የሚል ይጠንቀቅ» የሚለውንና ጴጥሮስ የወደቀው ሌሎች» ጥለውህ ቢሸሹም እኔ አላደርገውም» ባለበት ጊዜ መሆኑን አስታውስ (ማቴ. 26:33፤ 1ኛ ቆሮ. 10:12)።

ይህ ፈተና ደግሞ ብዙዎችን መንፈሳዊ ሰዎች አሸንፏል፥ ከዚህ ፈተና ካልሸሹ በመታገል ማሸነፍ አይቻልም (1ኛ ቆሮ. 6:18)። ሆኖም ሌሎች ሰዎች ባሉበት አካባቢ ወይም የበሩን መዝጊያ ክፍት በማድረግ ተቃራኒ ጾታዎችን ማገልገል ይቻላል።

• የበላይነትና የበታችነት ስሜት

በማናቸውም ጥሪና ሙያ ላይ ሆኖ ሲያገለግሉ በአገልጋይነት ልታወቅ ልታወቅ ማለትና የበላይነት አስተያየት ቀስ ብሎ ሕይወታችንን ሊገዛ ይችላልና ሊጠነቀቁ ይገባል። ይህም የሚመጣው ብዙ ሰው ከማገልገላችን የተነሣ የሰዎችን አስተሳሰብና ባሕርይ ቶሎ የማወቅ ችሎታችንን እያዳበርን ስለምንሄድ ነው።

በማገልገል ላይ እያለህ የበላይነት ስሜት ብቅ ሲል ወዲያውኑ ከሥጋ መሆኑን በማወቅ በኩራት ምክንያት ለሰይጣን ስፍራ እንዳትሰጥ ልብህን ወደ እግዚአብሔር መልሰህ ይቅርታ ጠይቅ። በሌላ አንፃር በአገልግሎት ላይ የበታችነት ስሜት እየመጣም በሕይወትህ ሊያስቸግርህ ይችላልና ኃይልን በሚሰጥህ በእግዚአብሔር በመተማመን ተበራታ።

• ምስጢርን ማውጣት

በአገልግሎትህ አጋጣሚ ስለምታማክረው ሰው ሁኔታ ብዙ ምስጢር ልታውቅ ስለምትችል ሰውየውን ካላስፈቀድህ ለሌላ መናገር የለብህም። ለሌላ ሰው ትምህርት ይሆናል ካልህ፤ የሰውየውን ሕይወት በማያደናቅፍ ስሙን፥ ቦታውንና የመላለሰውን ለውጠህ ለምሳሌነት ልትጠቀምበት ትችላለህ።

• ከልክ በላይ በአገልግሎት መጠመድ

ሰዎችን በችግራቸው ለመርዳት ሲሉ ከልክ በላይ የሚሠሩ ሰዎች ጤንነታቸው ሊታወስ ስለሚችል፥ የጤንነታቸው መታወክ ደግሞ ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው መታወክ ምክንያት ሊሆን ይችላል፤ ስለሆነም በመንፈሳዊ ነገር የሚያገለግል አልፎ አልፎ ካላረፈ ወይም ከአገልግሎቱ አሳቡን አንስቶ በሌላ ላይ ካላደረገ፥ ሽርሽር በእግሩ ካላደረገ፥ ኃይሉን እያጣ ራሱን ኪሣራ ላይ ይጥላል። ስለዚህ ከመንፈሳዊ ችግሮች ጋር ሳያቋርጡ ከመጋፈጥ ማረፍ ሊታሰብበት የሚገባ ነው። በሌላም በኩል

የአገልግሎት ብዛት ቤተሰብን ወደ መርሳትና ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረን የሚገባውን የግል የጥሞና ጊዜ ሁሉ ሊያጠፋ ስለሚችል በመጀመሪያ ለእግዚአብሔር፥ ከዚያ ለቤተሰብ ቀጥሎ ለሥራ፥ ቀጥሎ ለአገልግሎት በሚል ቅደም ተከተል መጠቀም ይበጃል።

- **ቃሉን በራስ ሕይወት ሳይለማመዱ ያንን እውነት ለሌሎች ብቻ እንደሚጠቅም አድርጎ መናገር**

ከዚህ አደጋ ለመዳን አንድ አገልጋይ ለሌሎች የሚጠቅሰውን ቃል በራሱ ሕይወት አስቀድሞ ማዋል አለበት። ለምሳሌ በጌታ ኢየሱስ ዘመን ፈሪሳውያን ራሳቸው በጣታቸው የማይነኩትን ለሰዎች ያሸክሙ ነበር። ስለሆነም ሌሎችን ከማስተማርህ በፊት በራስህ ሕይወት መለማመድ ይኖርብሃል። ይህ ሁሌ ላይሳካ ይችላል፤ ግን ሙከራ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

- **ተቻኩሎ አንድ መደምደሚያ ላይ መድረስ**

ለምሳሌ ሚስት መጥታ ስለ ባሏ ብትናገር የባልን ወገን ሳይሰሙ አንድ መደምደሚያ ላይ መድረስ ወይም ሁለት ሰዎች ቢጣሉና አንዱ ቀደሞ ሲናገር የእርሱን አሳብ ወስዶ ሌላውን የመኮነን አደጋ ያጋጥማል። ስለዚህ ሚዛናዊ ለመሆን እንዲቻል፤ ሌላውን ወገን ሳታናግር ወይም ሳታዳምጥ ተቻኩለህ መፍትሔውን አትጠቁም።

- **አሳበ-ግትርነት**

ለምሳሌ ለሁሉ ችግር ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና ጸሎት ብቻ መፍትሔ ነው ብሎ የመጠቆም ወይም ችግሩን አዳምጦ ያለመጽሐፍ ቅዱስ ንባብና ጸሎት መፍትሔው ይኽ ነው ብሎ የመሞከር አደጋን መከላከል አለብህ፤ ስለዚህ የነገሩን ሁኔታ እንደ ሰውየውና እንደ ችግሩ አይቶ በሚዛናዊ መንገድ መጠቀም ይረዳል።

- **ውጤት አልባነት ስሜት**

በምናገለግልበት ጊዜ ሁሉ ጥሩ ውጤት ያመጣል ብሎ ማሰብ አደገኛ ነው። ጌታችን ያንን ባለጠጋ ወጣት ሐብትህን ሁሉ ጥለህ ተከተለኝ ሲለው አዝኖ እምቢ ብሎ ሄደ የሚል ከመጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን። በሁኔታው ጌታ ኢየሱስ አዘነ እንጂ ራሱን በዚህ ምክንያት አልኮነነም።

አንድ አገልጋይ ልምዱን ሊያካፍል ይችላል፤ ሊጸልይለት፥ ቃሉን ሊያነብለት፥ ሊያስጠነቅቅ፥ ሊያደፋፍርም፥ ሊመክር፥ ሊመራ ይችላል፥

ግን ሰውየውን እንዲታዘዝ ሊያስገድደው አይችልም። ያማከርኸው ሰው መጨረሻ ላይ ራሱን ቢገድል፤ በዚህ አንተ ልትፀፀትና ራስህን ልትኮንን አይገባህም። ጌታችን ኢየሱስ አማከሮት ሳለ ምክሩን አልሰማ ብሎ ይሁዳ ያስቆሮቱ ራሱን መስቀሉን አስታውስ።

- ስንፍና

አገልጋይ ጊዜውን ቃሉንና ሌሎችንም ጠቃሚ መጻሕፍት በማንበብ እንዲሁም በመጸለይና በማጥናት ፈንታ፥ በሐሜት፤ ወረቀት በማገላበጥ ቁጭ ብሎ ሁልጊዜ በማለም ጊዜውን ሊያባክን ይችላል። ስለዚህ የምታገለግለው ሰው ባታገኝ–ቴፕ አዳምጥ፥ አዲስ መጽሐፍ አንብብ፥ ስለ አዲስ የአገልግሎት ዘዴ አስብ፥ ደቂቃዎችህን ጠብቃቸው። ሰዓታት ራሳቸውን ይጠብቃሉና። አለበለዚያ ጦርነት መሄድ ሲገባው፥ ነገሥታት ሁሉ ወደ ጦርነት ሲሄዱ በቤቱ ለመዝናናት በመቅረቱ የኦርዮን ሚስት ቤርሳቤህን እንደደፈረ እንደ ዳዊት በደፋር ኃጢአት ውስጥ መውደቅ ይመጣብሃል።

ተቀባይነት ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ

ተቀባይነት ለማግኘት ስትል እውነት የሆነውን በመናገር ፈንታ አንድ አዲስ ነገር ለመናገር መጓጓት፤ በሌሎች ከፍተኛ ግምት ለማግኘት ስትል የታላላቅ ሰዎችን ንግግር መቅዳት፤ ያልደረስህበትን እንደንደረስህበት አድርገህ ማውራት፤ ከሌላው በልጦ ለመገኘት ማለትም፤ በመረዳት ፈንታ የራስን አዋቂነት ለማሳየት መሞከር፤ አገልጋይነትህን ይፈትናል። በዚህ ፈንታ የምታማክረውን ሰው የእግዚአብሔርን ተቀባይነት እንዲያገኝ ወደ እግዚአብሔር መጠጋትን አሳየው ምክንያቱም አንተ ለሁሉም ችግር መፍትሔ የለህምና።

ቅናትና ምቀኝነት

አንድ ሰው በሌላ ሰው አገልጋይነት ለችግሩ መፍትሔ እንዳገኘ ሲነግረን፥ በውስጣችን የቅናት ስሜት ሲሰማን፤ ወይም እኔ የሌለኝ እርሱ ምን? አለው ብለን የምንናገር ከሆነ የቅናት በሽታ አለብን ማለት ነው። ያንን ሰው አንተም ማመስገን ሲገባህ ልክ ነው የምትለው ግን እኮ እገሌ እንዲህ ያለ ደካማ ጎን አለበት ብለህ ስትናገር በቅናትና ምቀኝነት ፈተና ውስጥ ይጥልሃልና ከዚህ አባባል ራስህን ጠብቅ፥ ይልቁንም ጌታ በአገልጋዩ በመጠቀሙ እግዚአብሔርን አመስግን። እዚህ ላይ ቃየል አቤልን የገደለው እግዚአብሔር የአቤልን መስዋዕት

ስለተቀበለና የእርሱን ስለናቀ ነው፤ ግን እኮ አቤልን ከመግደል ይልቅ፤ የራሱን ሕይወት ቢመረምር እርሱም ንስሐ ገብቶ ከመቅበዝበዝ ሕይወት ያመልጥ ነበር። ንጉሥ ሳኦልም ዳዊት አሥር ሺ ገደለ ሲባል ለእኔ አንድ ሺ ሰጥተው እርሱን አስበለጡት ብሎ ቢቀናም ዳዊት ዙፋኑን ከመውረሱ ሊያስቀር አልቻለም። ስለዚህ ቅናትን ምቀኝነትን የሥጋና የሰይጣን መሣሪያዎች መሆናቸውን በመገንዘብ በእነዚህ ፈተናዎች ስትወድቅ በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ ግባና በክርስቶስ ደም በእምነት ንጻ።

ራስን ማድነቅ

ራስን ማድነቅ ለራስ ክብር መስጠት ነው። አንድ ሰው በደንብ ነው የረዳሽኝ ሲል ልክ ነው ብለህ ከተቀበልህ በአንተ ውስጥ ሆኖ እርሱን የረዳው ክርስቶስ መሆኑን ረስተሃል ማለት ነው። ስለዚህ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ክብርን ለራስህ በመውሰድህ እግዚአብሔርን ታሳዝናለህ፤ ለሰው አንዳች ጠቃሚ ነገር ብታደርግ እግዚአብሔር በሰጠህ ስጦታ ነውና ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት አለብህ። ከእንደዚህ ያለ በራስ ከመመካት ለመውጣት ከፈለግህ ለእግዚአብሔር ጥበቃ በየቀኑ ራስህን አደራ ስጥ።

5. የመንፈስ አንድነት መጠበቅን እያንዳንዱ ምእመን ሊያስብበት ይገባል

ዛሬ በዓለም ዙሪያ በአገሮችና በሕዝቦች መካከል ጠብና የጠብ ወሬ ይሰማል። ሬዲዮኖችና ቴሌቭዥኖች ሲከፈቱ የሚደመጠው፥ ጋዜጦችና መጽሔቶች ሲነበቡ ይህ እውነት ይረጋገጣል። እርቅ ይደረግና ውሎ ሳያድር እርቁ ፈርሶ እንደገና የሕዝብ መጨራረስ ይታያል። ያ መንፈስ በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ አልፎ አልፎ ሲሠራና ዲኖሚኔሽኖች ከዲኖሚኔሽኖች፥ አገልጋይ ከአገልጋይ፤ ምእመን ከምእመን፤ እለመግባባት ሲፈጠር በዚህም ምክንያት አገልግሎቶች ሲዳከሙና የአካባቢ መሳለቂያ ቤተ ክርስቲያን ስትሆንና የክርስቶስ ስም ሲሰደብ መስማትና ማየት እጅግ ያሳዝናል።

የእኛ የአማኞች አንድነት የመጣው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ለእያንዳንዳችንና ለዓለም ሕዝብ ኃጢአት ዋጋ ለመክፈል ባፈሰሰው ደሙ ነው። በዘርና በጎሳ፥ በሐብትና በድህነት በጾታ፥ በእድሜ፥ በትምህርት በመሃይምነትና በመሳሰለው ተራርቀን የነበርነውን፥ ጌታ

ኢየሱስ በሥጋው አፍርሶ ሰላምን ሰጥቶናል። በዚያን ጊዜም ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቆን የእግዚአብሔር ቤተሰቦች አድርጎን እርስ በርሳችንም አስታርቆናል። ሁላችን በአንዱ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል፥ ያንኑ መንፈስ ደግሞ ሁላችንም ጠጥተናል (ኤፌ. 2፡13–19፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡13)።

ምንም እንኳ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ዴኖሚኔሽናል አሠራር ቢኖራትም፤ በእግዚአብሔር ፊት ያለችው አንዲት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናት፤ ይህችም ዓለም አቀፋዊ ቤተ ክርስቲያን፥ እውነተኛ አማኞች ሁሉ በመንፈስ አንድ የሆኑባት ናት። የተለያየ የዲኖሚኔሽን መጠሪያ ያለን ቢሆንም በእግዚአብሔር ዘንድ የምንታወቀው በእግዚአብሔር ፍቅር፥ በጌታ ጸጋ፥ በተሰጠን በእርሱ ልጅነት ስለሆነ ወደ መንግሥተ ሰማይ ስንሄድ ይህ የዲኖሚኔሽን ስም ይቀርና በእግዚአብሔር በተሰጠን ልጅነታችን አንድ አካል፤ አንድ ቤተሰብ ሆነን እንኖራለን።

ያም ስለሆነ፥ በኤፌሶን 4፡3 ላይ የመንፈስ አንድነትን ጠብቁ ብሎ የእግዚአብሔር ቃል የሚያዘውን በመጠበቅ በአንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር ጣር፥ በማንም ላይ ቂም አትያዝ፥ ፍርዱን ሁሉ ለእግዚአብሔር ስጥ እንጂ አትበቀል፤ ክርስቶስ የሞተለትን አንተ አትናቀው፤ ይልቁንም በኢየሱስ ዓይን እየው፤ በደልም ቢኖር እንኳ ይቅር በል።

«እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ» ...ብሎ ጌታ ኢየሱስ በየትኛውም ዲኖሚኔሽን ወይም ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያን ያለን ምእመናን አንድ እንሆን ዘንድ፥ ጌታ ኢየሱስ ፀልዮልናል (ዮሐ. 17፡18–23) ያ ጸሎት ደግሞ አንተንም ይጨምራል። ስለዚህ ክርስቶስ አንድ ያደረጋትን ቤተ ክርስቲያን ማንም በምንም ምክንያት መከፋፈል የለበትም፤ መከፋፈልን የምትዘራ ከሆነ ደግሞ ሌሎችን ታሰናክላለህ፤ «ከነዚህ ከታናናሾች አንዱን ያሰናከለ ፍርድ ይጠብቀዋል» ብሏልና ይህን ተግባር እንደ ቀላል ጥፋት አትየው። አንተ ተጎድተህ ባልንጀሮችህን ብትጠቅም እግዚአብሔር አንተን ይባርክሃልና የመንፈስ አንድነትን የመጠበቅ ትእዛዝን ተግተህ ጠብቅ፥ የሰላም አምላክም ይረዳሃል፤ ለሌሎች መሰናክል እንዳትሆንም ራስህን ለመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን አስገዛ።

ለተለየ አገልግሎት (ሚንስትሪ) እግዚአብሔር ቢጠራህ፥

ጥሪው ከርሱ መሆኑን እንዳች የግል ዓላማ ወይም ጥቅም እንዳላነሣሣህ አረጋግጠህ ቤተ ክርስቲያን ባርካ እንድትልክህ ጥያቄህን በትህትና አቅርብ። ስታገለግልም በሐዋ. 20፡24–35 የተጻፈው መመሪያ

ይሁንህ፤ ሆኖም ለእግዚአብሔር እንጂ ለማንም ተጠያቂ አልሆንም በማለት ከአጥብያ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ራስህን አታግልል፤ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳዳሪዎች ሳይሆን በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ይጠብቁ ዘንድ የሾማቸውን መንፈስ ቅዱስን አስብ። ሐዋርያው ጳውሎስ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን የወንጌል አገልግሎት ወደ ሩቅ አገሮች እየሄደ አስተምሮ ሲመለስ በየጌዜው ያደረገው ምሳሌ ይሁንህ። ከሚስዮናዊው ጉዞው በኋላ ለላካቸው ቤተ ክርስቲያን፥ ለአንጾኪያ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና በይሁዳ ላሉት ሐዋርያትም ሪፖርት ያቀርብ ነበር። (የሐዋ. 14፡26፡-28) ገላትያ 2፡1-10 ስለሆነም ተጠያቂነትህ ለእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያንም ጭምር መሆኑን አትዘንጋ በተጨማሪ በተለየ የአገልግሎት ጥሪ (ሚኒስትሪ) ስታገለግል አጥብያ ቤተ ክርስቲያንህ በየጊዜው ገንዘብና ቁሳቁስ ተንቀሳቃሽ ቋሚ ንብረትን ለአገልግሎትህ ተቀብለህ ስታስተዳድር ላታይህ ስለምትችል፤ ለአገልግሎትህ የምትቀበለውን ገንዘብንና ልዩ ልዩ ንብረትን፥ የመሳሰሉትን በቅርብ የሚቆጣጠሩ የቦርድ ወይም ሌላ የአዲት አካላት ኖረው አስተዳደርህንና ንብረቱን ቢቆጣጠሩ አገልግሎትህ ጤናማ ይሆናልና አስብበት፤ አጥብያ ቤተ ክርስቲያናትም እንዲህ ላለ ልዩ አገልግሎት ወይም ሚንስትሪ ምእመናን ሲጠሩ፤ ነገሩ ከእግዚአብሔር መሆኑን በጾምና ጸሎት በማረጋገጥ ሊባሩካቸውና ቀኝ እጃቸውን ሊሰጡአቸው ይገባል)። ምክንያቱም በይሁዳ ያሉት ሐዋርያት የጳውሎስን እና የበርናባስን ጸጋ አውቀው ቀኝ እጃቸውን ሰጥተዋቸዋልና (የሐዋ. 12፡3፤ ገላ. 2፡9)።

6. ክሐሰት ትምህርቶችና ከሐሰት አስተማሪዎች ራስህን ተከላከል

ድሮ በልጅነቴ ስንዴ በለሰለሰ ማሳ ላይ ከተዘራ በኋላ ማደግ ሲጀምር ስንዴውን የሚመስል ገበሬው ያልዘራው እንክርዳድ በመጀመሪያው ሳይታይ ቆይቶ ግን ስንዴው ከፍ ሲል ከስንዴው ፈጥኖ በቅሎና አድጎ ስንዴውን ሲሸፍን አይቻለሁ። ስንዴውና እንክርዳዱ የሚለዩበት አንድ ነገር ቢኖር በእጅህ ያፈራበትን ቦታ ስታሸው ስንዴውን የያዘው ተክል ፍሬ ያለበት ሲሆን እንክርዳዱ ያለበት ግን ፍሬ የሌለው መሆኑን ታረጋግጣለህ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ምዕራፍ 7፡ላይ «የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ» ያለው ከላይ ለጠቀስሁት የስንዴና የእንክርዳዱ ምሳሌ ጋር ተመሳሳይነት

አለው። ሐሰተኞች ነቢያት ወይም አስተማሪዎች የሚመጡት የበግ ለምድ ለብሰው ነው፤ ግን ነጣቂ ተኩላዎች ናቸው። ሐሰተኞች አስተማሪዎች የሚይዙት መጽሐፍ፥ ሽፋኑ መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆንም የራሳቸው መጽሐፍ፥ የራሳቸው ትምህርት አላቸው። ከመጽሐፍ ቅዱስ በከፊል ቢጠቅሱም የራሳቸውን አጀንዳ ይዘው ነው የሚመጡት። የሚናገሩት ቃላት በእግዚአብሔር ወይም በኢየሱስ ስም የተሸፈነ ቢሆንም የራሳቸው ዶክትሪን አላቸው። አመጣጣቸው ለመልካም ቢመስልም ተልእኮአቸው አማኝን ከክርስቶስ ኢየሱስ ለመለየት ወይም አባላትን ለማስኮብለልና የተልእኮአቸው ምርኮ ለማድረግ ነው። ስለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በእነርሱም አማካይነት ለእኛ «ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ» ሲል የተናገረው (ማቴ. 24፡4–5)።

የሐሰት ትምህርት የተጀመረው በኤደን ገነት ነው፤ ያም ሔዋን ጆሮዋን ለሰይጣን ከከፈተችበትና ከሰይጣን ጋር ድርድር በጀመረችበትና የእርሱን ቃል በተቀበለች ቀን ነው (ዘፍ. ምዕ. 3)።

በዚህ በዘፍጥረት ምዕራፍ ላይ <u>ሰይጣን ወይም የእርሱ ደቀ መዛሙርት የሆኑት የሐሰት አስተማሪዎች እንዴት አማኝን ወደ ሐሰት ትምህርት እንደሚያስገቡ አንዳንድ ነጥቦችን እንደሚከተለው እንመልከት</u> ።

- ሰይጣን ወይም የእርሱ ደቀ መዛሙርት ወደ ምዕመን ሲመጡ በአስፈሪ ሁኔታ ሳይሆን ትሁት መስለው በሽንገላ ነው (ቁጥር 1)።
- ጥያቄዎችን በማብዛትና፥ ምእመኑ መጽሐፍ ቅዱስን ወይም የነበረውን የደኅንነት እምነት እንዲጠራጠር ያደርጉታል (ቁጥር 1)።
- ለሰይጣን (ለደቀ መዛሙርቱ) ጥያቄ በእርሱ መንገድ ሄዶ መመለስ ለእርሱ ስፍራ መስጠትና እግዚአብሔር ባልተናገረው ላይ ቃል ወደ መጨመር ያደርሳል (ቁጥር 3)።
- ለሰይጣን (ለደቀ መዛሙርቱ) ቃል ጨምሮ መናገር በእግዚአብሔር ላይ ጠላት የድፍረት ቃል እንዲናገር ወደ ክኅደት እንዲመራ ራስን ማመቻቸት ነው (ቁጥር 4–5)።
- ለእርሱ ከህደትና ሽንገላ ጆሮ መስጠት በመጨረሻም እንደ እግዚአብሔር አምላክ ነኝ፥ መንፈስም ነኝ በማለት ለመታበይና የእግዚአብሔርን ቃል በቀጥታ ወደ መጣስ ያደርሳል (ቁጥር 6)።

- የእግዚአብሔር ቃልን ጥሶ ሰይጣንን ወይም የእርሱን ደቀ መዛሙርት የሚሉትን ማድረግ ደግሞ ወደ ክብር ሳይሆን ወደ ሐፍረት፥ ወደ ራቁትነት፥ ወደ ፍርሃት፥ ወደ ውርደት፥ ፀጋን (በረከትን) ወደ መገፈፍ ያደርሳል (ቁጥር 7-8፥ 24)።

<u>በዘጸአት ምዕራፍ 7 እና 8 ደግሞ የሰይጣንንና ወይም የሐሰት አስተማሪዎችን ወይም የሐሰት ነቢያትን ተጨማሪ ማታለያ መንገዶችን እናያለን።</u>

በእግዚአብሔር ትእዛዝ በሙሴ አማካይነት አሮን በትሩን ሲጥል እባብ እንድትሆን ሲያደርግ የወንዝን ውኃ በበትሩ ሲመታ ውኃው ወደ ደም እንዲለወጥ ሲያደርግ፥ እንዲሁም በውሆች ላይ በትሩን ሲዘረጋ ጓጉንቸሮች እንዲወጡ ሲያደርግ የግብጽ ጠንቋዮች በእግዚአብሔር ኃይል እስኪሸነፉ ይህንኑ ሁሉ እንዳደረጉ ሰይጣንና መልእክተኞቹም የማስመሰል ተአምር ይሠራሉ (2ኛ ቆሮ. 11፡13-15፤ ማቴ. 24፡24-25) ስለዚህ ነው በ1ኛ ዮሐ. 4፡1 «ወዳጆቼ ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና» የሚለው?። ብዙ ሰዎች ደግሞ ከእውነት ይልቅ ሐሰትን እንደሚከተሉ የነቢዩ ኤልያስንና የ450 የብኤልን ነቢያት 400 የማምለኪያ ዐፀድን፥ ነቢያት በድምሩ 850 የሐሰት ነቢያትን እንዲሁም እነርሱን የተከተሏቸውን የእስራኤልን ሕዝብና መሪዎች ለብኤል ካልሰገዱት 7000 ምእመናን ጋር በ1ኛ ነገሥት 18 እና 19 የምናነበው።

<u>በይሁዳ መልእክት ላይ የሐሰት አስተማሪዎች ጠባይና ተግባር በግልጽ ተቀምጦ እናያለን። ከዚህ መልእክት የሚከተሉትን በማጤን የሐሰት አስተማሪዎችን ማንነት ማወቅ ይቻላል።</u>

- በምእመናን ማኅበር ሐሰተኞች ሾልከው ይገባሉ (ቁጥር 4)።

- የአምላካችንን ፀጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ (ቁጥር 4)።

- ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ የጌታ ኢየሱስን አምላክነት፥ በሥጋ ከድንግል ማርያም መወለዱን፥ ሞቱን፥ በፀጋው ሰዎች መዳናቸውን፥ ትንሣኤውን፥ ዳግም ምጽአቱን ይክዳሉ (ቁጥር 4)።

- እያለሙ ሥጋቸውን ያረክሳሉ እንደነዚህ ያሉ በአብዛኛው በራዕይና በመገለጥ ተመርተናል ብለው ትምህርታቸውን በማስተማር ሥጋቸውን የሚያረክሱ ናቸው (ቁጥር 8)።

- ሥልጣን ያላቸውን ሁሉ ይጥላሉ፥ ይሳደባሉም (የአብን፥ የወልድን፥ የመንፈስ ቅዱስን ሥልጣንና የቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን ይክዳሉ፥ ይሳደባሉም)። ማንም ከእኛ በላይ ወይም የተሻለ የለም ይላሉ (ቁጥር 8-10)።

- እንደ ቃየል በፀጋ የመዳንን ወንጌል ከደው በምግባር በመደገፍ የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ይጠላሉ፥ ቢቻላቸው ሊገድሉ ይፈልጋሉ (ቁጥር 11)

- እንደ ምዋርተኛው በለዓም የግል ጥቅማቸውን በማካበት ለስሕተት ራሳቸውን ሰጥተዋል (ቁጥር 11)።

- እነ ቆሬ ሙሴንና አሮንን እንደተቃወሙ የቤተ ክርስቲያንን አገልጋዮች (ሽማግሌዎች) ሥልጣንና ትምህርት ሁሉ ይቃወማሉ (ቁጥር 11) (ገላ. 4፥ 17፤ ዘኅልቁ 2፥ 1-9፤ 2ኛ ጢሞ. 4፥3-4፤ ዘኍልቁ 31፡16፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡14-15)

- በፍቅርና በኅብረት ላይ ክፍፍልና መለያየት እንዲኖር ያደርጋሉ፤ በፍቅር የሚደረገውን ማኅበር ወይም ግብዣ እንኳ ይነቅፋሉ (ቁጥር 12) (1ኛ ቆሮ. 11፡17-22፤ ሮሜ 16፥ 17 ና 18)።

- ስለ ምእመናን መመገብና መጠበቅ ግድ የሌላቸው በምእመናን መደናቀፍ ራሳቸውን የሚንከባከቡ ናቸው (ቁጥር 12) (ሕዝ. 34፡2-6፤ ዮሐ. 21፡15-17፤ 1ኛ ጴጥ 5፥2)።

- በውጭ ሲታዩ መንፈሳዊነትና በረከት እንዲሁም በጎ ነገር የሚገኝባቸው ይመስላሉ፤ ግን ቀርቦ ላያቸው ባዶ ናቸው በአዳዲስ ትምህርት የሚወሰዱና ከነፈሰው ጋር የሚነፍሱ ናቸው (ቁጥር 12) (ኤፌ. 4፡14)።

- ፍሬ የማያፈሩ በሚያስተምሩትና በሚያደርጉት ተግባር የሞቱ ናቸው (ቁጥር 12)

- አረፋ እስኪደፍቃቸው ስለራሳቸው ብዙ የሚያወሩና የሚከራከሩ ጨካኞች ለመንጋው የማያዝኑ ናቸው፤ ግን ታይተው የሚጠፉ ናቸው (ቁጥር 13) (ኢሳ. 57፡20፤ ሮሜ 1፡32፤ 2ኛ ጢሞ 2፡16-18፤ የሐዋ. 20፡29-30)

- ዋና ምልክታቸው አንድ ቦታ ፀንተው የማይገኙ ከአንዱ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው ከአንዱ እምነት ወደ ሌላው እያሉ

ዘመናቸውን በማሳለፋቸው እንደሚንከራተቱ ከዋክብት ይቆጠራሉ (ቁጥር 13)።

ስለዚህ በሥላሴ ትምህርትና በመጽሐፍ ቅዱስ ታማኒነት እውነት ለመቆምና፥ ሰው ካለ እግዚአብሔር ምሕረት ራሱን ማዳን የማይችልና ሊድን የሚችለው ከኃጢአቱ ንስሐ በመግባትና በጌታ ኢየሱስ በማመን መሆኑን በተቀበልህበት ሐቅ ላይ ተደግፈህ ለመኖር፥ ራስህን ከሐሰተኛ ትምህርቶችና ከሐሰተኛ አስተማሪዎች ለመጠበቅ ትጋ፤ በእግዚአብሔር ጥበቃ ላይ ተደገፍ እንጂ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ፤ ለዚህም እግዚአብሔር ይርዳህ።

7. የአገልግሎት ስጦታዎች፥ የጸጋ ስጦታዎችና የመንፈስ ፍሬ በአንድነት ሲሠሩ እድገትን ለቤተ ክርስቲያን ያመጣሉ

የጸጋ ስጦታዎች ብዙ ናቸው (ኤፌ. 4፡11፤ 1ኛ ቆሮ. ምዕ. 12፡4-11፥28፤ ሮሜ 12፡3-7፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡10-11)

<u>ስለ መንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች የሚከተሉትን አንዳንድ ነገሮች</u> እንላለን

- <u>የስጦታዎቹ ምንጭ</u> እያንዳንዱ የሥላሴ አካል እግዚአብሔር አብ ሮሜ 2፡3 እግዚአብሔር ወልድ ኤፌ. 4፡7-8፤ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ (1ኛ ቆሮ. 12፡7-8፡11) ነው።
- <u>ስጦታዎቹን የሚሰጡት</u> አማኝ እንደፈለገ ብቻ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ እንደፈቀደው ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡7፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡28-31 14፡1)።
- <u>የስጦታዎቹ ዓላማዎች</u> ደግሞ ለወንጌል ስርጭት የሐዋ፡ 1፡8 ለጋራ ጥቅም 1ኛ ቆሮ. 12፡7 እርስ በርስ ለመተናነጽ ነው (1ኛ ቆሮ. 14፡26)።

መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከአብና ከወልድ ጋር ብእኩል መልክ (ማቴ. 28፡19፤ 2ኛ ቆሮ. 13፡14) ተገልጾ የኢየሱስ መንፈስ እና የእምላካችን መንፈስ ተብሎ ተጠርቷል (የሐዋ. 16፡7፤ 1ኛ ቆሮ. 6፡11) ድንግል ማርያም እንድትወልድ የጸለለላት፥ መጽሐፍ ቅዱስን፥ በርሱ ተነድተው እንዲጽፉ ያደረገና በዓለም መፈጠር ላይ የተሳተፈ በመሆኑ አምላካዊ ሥራዎችን ፈጽሟል። (ሉቃስ 1፡35፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡21 ዘፍጥ. 1፡2 ኢዮብ 33፡4 መዝ. 104፡30) እርሱ ወደ እውነት ሁሉ ይመራል፤ በኃጢአት ይወቅሳል፤ ተአምራትን ይሠራል፤ ያማልዳልም (ዮሐ. 16፡13፤ 16፡8፤ የሐዋ. 8፡39፤ የሐዋ. 16፡6-18፤ ሮሜ 8፡26)

ሀ) <u>በኤፌሶን 4፡11 የተጻፉትን የአገልግሎት ስጦታዎች የሚያሳዩት</u> 5 ዓይነቶች አገልጋዮችንና አገልግሎቶችን ነው፤ እነዚህም ሐዋርያት፥ ነብያት፥ ወንጌል ሰባኪዎች፥ እረኞች እና አስተማሪዎች ናቸው።

አገልጋዮች ደግሞ በስጦታቸው ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ የተሰጡ ናቸው። (ኤፌ. 2፡20፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡28) እስቲ የያንዳንዳቸውን ቃል ፍችና አገልግሎት እንመልከት።

- ሐዋርያነትና ነብይነት ዛሬ አለ ወይ?

<u>ሐዋርያ</u> :- የተላከ ወይም መልእክተኛ ማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሃይማኖታችን /የእምነታችን ሐዋርያ/ ሆኖ ከአባቱ ከአብ ወደ ምድር የተላከ ነበር። (ዕብ. 3፡1፤ ዮሐ. 17፡18፥ 20፡21-22/ እርሱ ደግሞ በበኩሉ የመረጣቸውን 12 ደቀ መዛሙርት በኋላም ሐዋርያት የተባሉትን ወደ ዓለም ላካቸው ከሐዋርያት ጋር የሚቆጠር ሰው ክርስቶስን የተከተለና ትንሣኤውን ያየ መሆን ነበረበትና ማቲያስ በይሁዳ የአስቆሮቱ ምትክ ተመረጠ የሐዋ. 1፡8፥ 21-26 ከእነዚህ መካከል ሌሎች ሐዋርያት ተብለው ተጠርተዋል፤ የጳውሎስ፥ የአንዲራኒቆንና ዩልያን በአሥራ ሁለቱም የታወቁ ሐዋርያት ነበሩ (ገላ. 1፡1፥ 1ኛ ቆሮ. 9፡1፥ የሐዋ. 26፡16-18፤ ገላ. 2፡9፤ ሮሜ. 16፡7)። የሐዋርያት ሥራቸው ቃሉን መስበክ፥ ማስተማር፥ ቤተ ክርስቲያንን ማስተዳደር ማደራጀት የክርስቶስን ትንሣኤ መመስከር፥ የጌታን ራት ሥርዓት በማስፈፀም የመሪነትን ስፍራ መውሰድ ነበር። ለችግረኞች የሚዋጣውን ገንዘብ ያከፋፈሉም ነበር። ምእመናን ሲያጠፉም ቅጣትን ይወስኑ ነበር። በእነርሱ እጅ መጫንም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ይሰጡ ነበር። ከጌታ ላገኙትም ስልጣን ማረጋገጫ ርኩስ መናፍስትን በኢየሱስ ስም ያስወጡ፥ በሽተኞችን በጌታ ኢየሱስ ስም ይፈውሱ ነበር። በእምነት ጉዳይ አለመግባባት ሲነሣም በመመካከር በመንፈስ ቅዱስ በመመራት መወሰድ ስለነበረበት እርምጃ ይወስኑ ነበር። (የሐዋ. 2፡24፤37-42፤ 3፡4-26፤ 4፡32-35፤ 5፡1-16) ሆኖም ቤተ ክርስቲያናት እያደጉና ምእመናንም በየአገሩ እየተበተኑ ሲሄዱ ሥራውም እየበዛ ሲሄድ ለሌሎች ውክልናን በመስጠት እነርሱ ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል፥ የተበተኑትን ቅዱሳንን በመጎብኘት ላይ እያተኮሩ የተቀረውን ሥራ ለታመኑ ሰዎች እየሾሙ እንደሰጡ በሐዋርያት ሥራ 6፡2፤ ቲቶ 1፡5 በሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ ይነበባል።
<u>ዛሬ የሐዋርያት ማዕረግ የሚሰጣቸው በቤተ ክርስቲያን ይኖራሉ ወይ?</u> ለሚለው ጥያቄ ምእመናን በሁለት ቦታ ይከፈላሉ። ይህ የሐዋርያነት አገልግሎት በዚያ በሐዋርያት ዘመን አክትሟል የሚሉና ሌሎች ደግሞ

በየቦታው እየሄዱ ወንጌልን በመስበክ ቤተ ክርስቲያን እንድትመሠረት ያደረጉና የሚያደርጉ ወንጌላውያን (ሚስዮናውያን) ወይም ሽማግሌዎች ሐዋርያት ተብለው ይጠራሉ የሚል ነው። ጉዳዩን ከጌታ ኢየሱስ ጋር የነበረና የትንሳኤው ዓይን ምስክር የሆነ ከሚለው እንፃር ካየነው በዛሬ ዘመን እንደጥንቱ ሐዋርያት ተብለው በተመሳሳይ ደረጃ የሚቆጠሩ የሉም፤ ነገር ግን ሐዋርያት ይሠሩ የነበሩትን ዓይነት አገልግሎት በተመለከተ የሚታይ ከሆነ ደግሞ ዛሬም ያ ጸጋ በቤተ ክርስቲያን አለ ማለት ይቻላል።

ነብያት ፦ በብሉይ ኪዳን ዘመን ቃሉንና ወቅታዊ የሆኑ ፖለቲካዊ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን በሚመለከት መልእክት ከእግዚአብሔር ተቀብለው ለሕዝብ የሚናገሩ ነበሩ። ቃሉ አንዳንድ ጊዜ በራእይ፥ በሕልም፥ በመልአክም ይገለጥላቸው ነበር (ዘኁል. 12:6፤ ዳን. 10:11 የሚናገሩትም የእግዚአብሔር ውሳኔ ስለሆነ ስለ መንግሥታት ስለ ሰዎች፥ ስለ ኃጢአት ወደፊትም ስለሚሆኑት ድርጊቶች ነበር። በአዲስ ኪዳን ዘመንም ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡት ነብያት የሚመጣውን በመግለጥ (የሐዋ. 11:27-28፤ 21:10-11፤ ራእይ 1:19) ቤተ ክርስቲያንንም በመምከር በማጽናናትና በማነጽ (የሐዋ. 15:32፤ 1ኛ ቆሮ. 14:3-4) አገለገሉ። እንዲሁም ምእመናን ለተወሰኑ አገልግሎት እንደተጠሩ በማስታወቅና ለዚያም አገልግሎት የሚያበቃ መንፈሳዊ ስጦታን እንዲያገኙ በመርዳት (የሐዋ. 11:27-28፥ 13:1-2፤ 1ኛ ጢሞ. 4:14) አገልግለዋል። እነዚህም ነብያት ከሐዋርያት ለጥቆ ተገልፀዋል (1ኛ ቆሮ. 12:28-31፤ ኤፌ. 4:11) ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረት ከጌታ ኢየሱስና ከሐዋርያት ቀጥሎ እነርሱ እንደነበሩ ይናገራል (ኤፌ. 2:20) እነዚህም ነብያት በግልም ሆነ በማኅበር ይሠሩ ነበር (የሐዋ. 11:27፥ 13:1፤ ራዕይ 19:10፤ 22:9፤ 1ኛ ቆሮ. 12:29)። እነዚህ አገልጋዮች ደግሞ ቃሉ በሙላት የነበረባቸው ነበሩ።

<u>ዛሬ በቤተ ክርስቲያን እንደነዚህ ያሉ ነብያት አሉ ወይ</u>? የሚለው በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ሁለት አመለካከቶች አሉ፤ ከነዚህ አንደኛው «ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል» የሚለውን በመጥቀስ መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ያለቀ ስለሆነ የነብያት አገልግሎት አብቅቷል የሚለው ነው፤ ሌላው አመለካከት ደግሞ ክርስቶስ ዳግም ሲመለስ ስጦታዎች ያቆማሉ የሚል ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር ሳይጋጭ ተጨማሪ ቃል ሳይጨምሩ፥ በብዙ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት የነብይነት ማዕረግ ወይም ስም ሳይሰጣቸው በአዲስ ኪዳን የተገለጡትን ዓይነት የመገንባት፥ የመግለጥና የማስጠንቀቅ አገልግሎቶችን የሚሰጡ እውነተኞች ምእመናን ዛሬም አሉ (የሐዋ.

9፡15-17፤ የሐዋ. 13፡1-2፤ 1ኛ ቆሮ. 14፡24-25፤ የሐዋ. 11፡27-28፥ 21፡10-11፤ 15፡32)። (የሐዋ. 2፡17-18፥ 19፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡4-5)

እንደዚህ ያለ ስጦታ ያላቸው አገልጋዮች ራሳቸው ስጦታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸውን ማሳወቅ ሲገባቸው፥ ቤተ ክርስቲያንም ስጦታቸው ለመሆኑ ካረጋገጠች ልትለያቸው ትችላለች (1ኛ ቆሮ. 14፡29-32) ነብያት በሚተነብዩበት ጊዜ በተራ እንዲናገሩና ለሽማግሌዎችም ሊታዘዙ ይገባቸዋል፤ ለነዚህ አገልጋዮች የትንቢት ቃልም ሲመጣላቸው ለግለሰብ ከሆነ ለዚያ ግለሰብ መንገር፥ ለሽማግሌዎች ከሆነ ለሽማግሌዎች መንገር ወይም ጽሮ ማቅረብ፥ ለጉባኤ ከሆነ በሚገባ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተመካክረው ሊናገሩ ይችላሉ። ይህ ዓይነት የነብይነት አገልግሎት የሚገኘው ከመንፈስ ቅዱስ ቢሆንም ስጦታው አለኝ ብሎ አንድ አገልጋይ ሳይቀመጥ ቃሉ በሙላት እንዲኖርበት መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና ማሰላሰል፥ በጸሎትና ራስን በቅድስና በመጠበቅ በራስ ማስተዋል ሳይደገፍ በመንፈስ ቅዱስ ሊመራ ይገባዋል (ዮሐ. 14፡21፤ ሉቃስ 11፡13፤ ሮሜ 8፡14)። በዚሁ አንፃር ደግሞ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ብለው ከልባቸው አመንጭተው፥ ሐሰትን የሚናገሩ ነብያት እንዳሉ አውቆ እውነተኛውን ከሐሰተኛው በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት መለየት በጣም አስፈላጊ ነው (1ኛ ዮሐ. 4፡1፤ 1ኛ ተሰ. 5፡19-22፤ 1ኛ ቆሮ. 14፡29-33)። እንደዚህ ያሉት አስመሳዮችም በተጨማሪ ከፍሬአቸውም ይታወቃሉ (ማቴ. 7፡15-23)።

ወንጌልን ሰባኪዎች /ወንጌላውያን/

ሰበከ ማለት ከጥንቱ የቃሉ ፍች፥ ላላመኑት የወንጌልን ቃል አወጀ ወይም ተናገረ ማለት ነው። (ማቴ. 4፡23፤ ማር. 1፡38፤ ሮሜ 10፡14፥ 15፡20፤ 2ኛ ጴጥ.2፡5፤ 1ኛ ቆሮ. 9፥16፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡2) ምእመናን ሁሉ የክርስቶስ ምስክሮች እንዲሆኑና የእርሱን በጎነት እንዲናገሩ የተጠሩ ቢሆንም በኤፌሶን 4፡11 መሠረት ባላመኑት መካከል ወንጌልን ለመስበክ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስና እንደ ወንጌላዊ ፊሊጶስ የሐዋ. 21፡8 በተለይ ለወንጌላዊነት የተጠሩ አሉ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማቴ. 9፡35፥ ተከታዮቹ ለምሳሌ ጳውሎስ በሮሜ. 15፡18-21 እና ወንጌላዊ ፊሊጶስን (በሐዋ. 8፡5፥ 12፥ 35፥ 40) ብናይ ሁሉም በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለማያቋርጥ ጊዜ ተቀምጠው ሳይሆን ወንጌል ወደ አልተሰበከበት ቦታ እየተዘዋወሩና ወንጌልና ወደ አልሰሙ ሰዎች በመሄድ የሰበኩ ስለሆነ፤ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን የወንጌላዊነት ስም ወይም ማዕረግ ተሰጥቶአቸው ያለውን ምእመን በማሰተማርና በመሳሰለው ብቻ የተቀመጡ ራሳቸውን ሊጠይቁና የቤተ ክርስቲያን

ሽማግሌዎች ስሙን ሲሰጧቸው ቃሉ እንዲሚናገረው የምሥራቹን ቃል ወደ አልሠሙት ለማሰማራት ከሆነ በእኔ አስተያየት ቢያሰማሯቸው ጥሩ ነው። ካልሆነ ስማቸው ከግብራቸው ጋር ካልተጣጣመ ለአገልጋዮችም ሆነ ለተገልጋዮች ግራ የሚያጋባ ይሆናል።

እዚህ ላይ ስለ ራዕይና ድርጊት የተፃፉ አባባሎች ላነሣ እወዳለሁ። «ራዕይ ያለ ተግባር ምኞት ነው። ተግባር ያለ ራዕይ ደግሞ ውሸንብር ነው» የሚል ነው። ስለዚህ ስምና ተግባር ቢጣጣሙ መልካም መሆኑ የሚያጠራጥር አይመስለኝም። ይህም ስለተባለ የወንጌላዊ ተግባሩ ወደ መጋቢነትና ወደ አስተማሪነት ሊለወጥ ወይም የመጋቢውና የአስተማሪው አገልግሎት ወደ ወንጌላዊነት ሊለወጥ አይችልም፤ ማለቴ አይደለም፤ ይህንንም የምናየው ከጢሞቴዎስ አገልግሎት ነው (2ኛ ጢሞ. 4፡5)። ጢሞቴዎስ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ የወንጌላዊነት /ሚስዮናዊነት/ አገልግሎት ካገለገለ በኋላ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያንም ለተወሰኑት ጊዜያት ተቀምጦ አደራጅ ሆኖ ሠርቷል (1ኛ ጢሞ. 1፡3-4)። ሆኖም ወንጌላውያን የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ስላልሆኑ በተጠሩበት ጥሪ ላይ ብቻ ቢያተኩሩ ጥሩ ነው።

እረኞች ወይም መጋቢዎች

እረኞችን ወይም መጋቢዎችን በሐዋርያት ሥራ 20፡17 እና 1ኛ ጢሞ 5፡17 የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ይላቸዋል። በሐዋ. 20 በቁጥር 28 ደግሞ ጳጳሳት ወይም የመንጋው ጠባቂዎች ይላቸዋል። ጴጥሮስም በ1ኛ መልእክቱ 5፡1-4 ላይ ሽማግሌዎችን እረኞች ወይም የእግዚአብሔር መንጋ ጠባቂ እንደሆኑ ይናገራል። በቲቶ 1፡5-7 ላይ ደግሞ ኤጲስ ቆጶስ ይላል። የእረኞች ዋና ሥራዎች፡- የእረኞች ቀዳሚ አገልግሎት ምዕመንን በጌታ ቃል እንዲያድጉና እንዲፀኑ በየእሑዱና በሌሎችም ቀናት ማስተማር፤ ይህንኑ ትምህርት ለማጠናከር የሰንበት ትምህርት ቤቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችን ማቋቋም ነው (ሕዝ. 34፡2፤ ዮሐ. 21፡15-17፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡2፤ ኤፌ. 4፡15)።

ቀጥሎም የመንፈስ አንድነት በአገልጋዮችና በምእመን መካከል መጠበቁን ማረጋገጥና ከባድ ችግሮች ሲያጋጥሙ አስቀድሞ በጉዳዩ ላይ በጸሎት የመንፈስ ቅዱስ መሪነትን በመሻት የሚመለከታቸውን ወገኖች ሰብስበው በማነጋገር፥ ከቃሉም ጋር በማመሳከር፥ በአስተዳደር ጉባኤ መፍትሔ መስጠት ነው (ኤፌ. 4፡2-3፤ የሐዋ. 15፡1-29)። እናት አባት የሌላቸውን፥ ባሎች የሞቱባቸውንና ሌሎችንም ችግረኞች በቤተ ክርስቲያን መረዳታቸውን መከታተል ይጠበቅባቸዋል (ገላ. 6፡10)። የቤተ ክርስቲያንን አባላት በየስጦታቸው እንዲያገለግሉ ማበረታታትና

ሁሉም በአግባቡና በሥርዓት መፈጸሙን መከታተል ይኖርባቸዋል (1ኛ ቆሮ. 12፡28፤ 14፡40፤ ሮሜ 12፡6-8፤ 1ኛ ጢሞ 4፡14)። ምእመናንን ከሐሰት ትምህርትና ከሐሰተኞች መጠበቅም ሊዘነጉት የማይገባ ነው (የሐዋ. 20፡28-30፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡5፤ በ1ኛ ጢሞ. 5፡17) በተጨማሪ ሽማግሌዎች በመልካም ምእመኑን የሚያስተዳድሩና ስጦታ ካላቸው ደግሞ በመስበክና በማስተማር ቢያገለግሉ መልካም ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡28፤ ሮሜ 12፡8፤ 1ኛ ጢሞ 5፡17)። እረኞች (ሽማግሌዎች) ለቤተሰባቸው፥ ለምዕመኑና ላላመኑ መልካም ምሳሌ መሆን አለባቸው (1ኛ ጢሞ. 3፡4-7፥ 5፡8፤ ቲቶ 1፡5-9፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡2-3) ሲያገለግሉም የእነርሱ አለቃ የሆነ እረኛ ጌታ ኢየሱስ እንዳለና ከእርሱ ለአገልግሎታቸው የማያልፈውን የክብር አክሊል እንደሚቀበሉ ማወቅ አለባቸው (1ኛ ጴጥ. 5፡4፤ ዕብ. 13፡20-21፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡25፤ ዮሐ. 10፡1)።

ስለሆነም ከውጭ ለመተዳደሪያቸው እየሠሩ (የሐዋ. 20፡33-34) በትርፍ ጊዜአቸው የሚያገለግሉ ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ኃላፊነቱን ቢወስዱም «ከእነርሱም መካከል የመስበክና የማተማር ስጦታዎች ያሏቸው ደግሞ በተጨማሪ በእነዚህ ስጦታዎችም ያገለግላሉ። መጋቢዎች ደግሞ ሙሉ ጊዜአቸውን ሰጥተው ለምእመኖች መንፈሳዊ ሕይወት የሚጠነቀቁና ነፍሳቸውን በመንፈሳዊ ምግብ የሚያገለግሉ ናቸው። ይህም በመሆኑ ሽማግሌዎችና መጋቢዎች ተደጋግፈው መሥራታቸው ለቤተ ክርስቲያን እድገት በጣም ይረዳል። አስተዳደራዊ መዋቅርን በተመለከተ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ በአብዛኛው ሁለት አሠራሮች አሉ፤ አንደኛው አንድ መጋቢ የቤተ ክርስቲያን የበላይ ተመልካች ወይም ተጠሪ ሆኖ ሌሎች ከሥሩ በሽማግሌነት ወይም በዲያቆንነት የሚያገለግሉበት ሲሆን፤ ሁለተኛው ቤተ ክርስቲያን በሽማግሌዎች ጉባኤ የምትተዳደር ሆና ከመካከላቸው አንዱ ሽማግሌ በሰብሳቢነት የሚመራበትና መጋቢው ግን ለዚህ ሽማግሌዎች ጉባኤ ተጠሪ የሆነበት አሠራር ነው። በእኔ አስተያየት ቤተ ክርስቲያን በአንድ አገልጋይ ከምትመራ በቡድን (በቲም) ሆኖ መጋቢ ወይም መጋቢዎች ከሽማግሌዎች ሥር ሆነው ቢሠሩ ይመረጣል እላለሁ። ሆኖም መጋቢው ወይም መጋቢዎች የሽማግሌዎች ጉባኤ ድምፅ ያለው ወይም ያላቸው አባል ወይም አባላት ሆነው መሥራታቸው ጠቃሚነት አለው።

<u>አስተማሪዎች</u> :- ኤፌ. 4፡11፤ የሐዋ. 13፡1 የማስተማር ስጦታ ከትንቢት ስጦታ ይለያል። (1ኛ ቆሮ. 12፡28-29፤ ሮሜ 12፡7) ነብይ ቃሉን የሚተነብይ ሲሆን አስተማሪው የተተነበየውን ቃል የሚያብራራና በትምህርት መልክ የሚያስቀምጥ ነው፤ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ከምትኖርበትና ከምትመሠክርበት ሁኔታ ጋር በነቢያት የተገለፀውን

ማዛመድ ነው። አስተማሪዎች ተከታታይና አንድ ወጥ የሆነ ትምህርት ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ናቸው። አስተማሪዎች ማስተማር ብቻ ሳይሆን የሚያስተምሯቸውን ምእመናን የሚወዱ መሆን አለባቸው፤ ስለሆነም የአስተማሪዎች አገልግሎት የጌታ ሕዝብን በክርስቲያናዊ መንገድ እንዲመሩ በቃሉ ማበረታታትና በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያለውን እውነት በሕይወታቸው ማሳየት ነው

ማጠቃለያ ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ ወንጌላውያን፥ እረኞችና አስተማሪዎች ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡት በጌታ ኢየሱስ ሲሆን ይህንንም ያደረገበት ዓላማዎቹ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ፥ ምእመናንን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ለማዘጋጀት፥ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ በእምነት ወደሚገኘው አንድነት ደርሰን፥ በክርስቶስ ሙሉ ሰው እንድንሆንና የታላቁን የወንጌል ስርጭት ተልእኮ እንድንወጣ ነው፤ እንዲሁም ምእመናን በአሳሳች ትምህርት እንዳይወሰዱ ሲሆን ይልቁንም ሁላችን ራስ የሆነውን ክርስቶስን ለመምሰል በሁሉ ነገር እንድናድግ ነው (ኤፌ. 4፡11-15)።

ለ) በ1ኛ ቆሮ. 12፡4-11 የተጻፉት የጸጋ ስጦታዎች- ስማቸውና የቃሎቹ ፍችዎች

<u>የመግለጥ ስጦታዎች</u> የጥበብ ቃል፥ የእውቀት ቃል፥ መናፍስትን መለየት ሲሆኑ

ጥበብን መናገር

- የመናገር ስጦታ ነው
- (ጥበቡ የሚገለጠው በትምህርት-በመልእክት፥ በምክር ውስጥ ሊሆን ይችላል።)
- መንፈስ ቅዱስ ወቅታዊ በሆነ መንገድ ራሱን በመግለጽ በአገልጋዩ የሚሠራበት መንገድ ነው።
- በወቅቱ ለማጽናናት፥ ለመምከር፥ የመፍትሔ ቃል ለመስጠት፥ በወቅቱ የውሳኔና የስምምነት ቃል ለማስተላለፍ ይሆናል። በሐዋ. ምዕ 15 ላይ የተላለፈው የውሳኔ ሃሳብ ለምሳሌነት ሊያገለግል ይችላል።

እውቀትን መናገር

- ለማያዊና መንፈሳዊ እውቀት ነው
- ምስጢርን የመግለጥ ስጦታ ነው 1ኛ ቆሮ. 13፡2

- ስለ ግለሰብ ቤተ ክርስቲያንን ወዘተ. በተፈጥሮ እውቀት የማይደርስበትን ነገር ከመንፈስ ቅዱስ በሆነ መገለጥ ማወቅና ማሳወቅ ነው።

- በሐዋ. 5፡1–11 ላይ ጴጥሮስ የተናገረው የሐናንያና የሰጲራን ጉዳይ እውቀትን የመናገር ምሳሌ ሊሆን ይችላል

- ከዚህ ላይ ልንጠቅስ የምንፈልገው የመገለጥ ስጦታ እየተባለ በአሁኑ ጊዜ በተለምዶ የሚጠራው እውቀትን መናገር ከሚለው ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል።

- አንዳንድ ጊዜ ይህንን በእውቀት መናገር ከትንቢት መናገር ጋር ቤተ ክርስቲያናት ያያዩዙታል። በማጠቃለያም የጥበብ ስጦታ ያለው የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገሮችን አውቆ የተለዩ ችግሮች በሚያጋጥሙበት ጊዜ በመፍታት እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ሰው ነው (1ኛ ነገ. 3፡16–28)። ይህ የጥበብ ቃል በጸሎት ይገኛል ያዕ. 1፡5፤ እግዚአብሔር ጥበብን እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል (ሉቃስ 21፡15፤ ሉቃስ 12፡12) ጌታ ኢየሱስ ጥያቄዎችን በጥበብ መለሰ (ማቴ. 21፡25፤ 22፡21) ዛሬ ሽማግሌዎች በሰማያዊ ጥበብ መምራት አለባቸው (1ኛ ቆሮ. 7፥ 12፥ 25፥ 40) ይህ ጥበብ ደግሞ በእውቀት ቃል ይገለጣል። እውቀትም በጥበብ ሥራ ላይ ይውላል፤ ስለሆነም ሁለቱ ተያይዘው ይሄዳሉ። የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ኃይል መግለጥ ለአስተማሪዎች በቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ልዩ እውቀት አለ። ይህ እውቀት የቤተ ክርስቲያንን እድገት ሊያግዝ የሚያስችል ነው። እንዲሁም እግዚአብሔር ስለ ግለሰብ፥ ቤተሰብ፥ ቤተ ክርስቲያን፥ ስለ አገርና ሕዝብ የሚናገረውን አውቀው ሊናገሩ ይችላሉ።

<u>የመናፍስትን መለየት ስጦታ</u> ደግሞ ከእግዚአብሔር የሆነውንና ከሰይጣን የሆነውን መንፈስ ለመለየት መቻል ነው (የሐዋ. 5፡11፤ የሐዋ. 8፡23፤ የሐዋ. 16፥16–18)።

<u>የኃይል ስጦታዎች</u> – እምነት፥ ፈውስ፥ ተአምር ማድረግ ሲሆኑ የእምነት ስጦታ ያለው ሰው ለመዳን ካገኘው እምነት በተጨማሪ እግዚአብሔር በሰዎችና በዓለም ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ መግባት እንደሚችልና ሊገባም ፈቃደኛ እንደሆነ እምነት ይኖረዋል። 1ኛ ነገሥ. 18፡30–38፤ የሐዋ. 3፡4–16፤ ማቴ. 17፡20

<u>የፈውስ ስጦታ</u>

- አንዱ ለሌላው ፈውስ መጸለይ ይችላል ያዕ. 5፡16።

- ሽማግሌዎችና የቅዱሳን ጉባኤ ለታመሙት በመጸለይ ፈውስ ይሆናል ያዕ. 5፡14-15፤ ማር. 16፡18

- ሆኖም የፈውስ ስጦታ ያለው ለሕመምተኞች ልዩ ሽክምና ራዕይ ኖሮት በእምነት ሊጸልይ ይችላል የሐዋ. 8፡6-7፤ 28፡8-10።

<u>ተአምር የማድረግ ስጦታ</u>

የዚህ ዓይነት ተአምር እንዲደረግ እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ሰው፥ ከተፈጥሮ ውጭ የሆነውን በእግዚአብሔር ኃይል ይገልጣል፤ ሆኖም ይህ ስጦታ በሁሉም ቦታ፥ ለሁሉም ሰው፥ በሁሉም ጊዜ የሚሰጥ አይደለም (የሐዋ. 5፡15፤ ዮሐ. 14፡12፤ የሐዋ. 9፡40፤ 20፡10፤ 19፡11-12)

<u>የመናገር ስጦታዎች</u> ትንቢት መናገር፥ በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፥ ልሳኖችን መተርጎም ናቸው።

<u>የትንቢት ስጦታ</u> በሁለት ይከፈላል፤ አንደኛው የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅ ሲሆን፥ ሌላኛው በወቅቱ ለግለሰብ፥ ለቤተሰብ፥ ለቤተ ክርስቲያን፥ ለአገርና ለሕዝብ ከእግዚአብሔር መልእክት የመቀበልና የማስተላለፍ ስጦታ ነው። እንዲሁም ማጎበሩን ለማነጽ፥ ለመምከርና ለማጽናናት የሚረዳ ስጦታ ነው (1ኛ ቆሮ. 14፡3)።

<u>የልሳን ስጦታ</u> ምእመኑ በማያውቀው ቋንቋ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመርቶ በመንፈስ የተቀናበሩ ቃላትን የመናገር ስጦታ ነው።

<u>በልዩ ልሳን የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ</u> ደግሞ በልዩ ልሳን የተነገረውን ግልጽ ማድረግ የሚያስችል ስጦታ ነው።

የእያንዳንዱን ስጦታ መዘርዘር ቢጠቅምም ዛሬ በቤተ ክርስቲያናት መካከል ብዙ አከራካሪ የሆኑቱን ስጦታዎች ብቻ አይተን እንዴት በሥራ ላይ መዋል እንደሚችሉ አንዳንድ ግንዛቤዎችን ከዚህ ቀጥሎ እናስቀምጣለን።

• የፈውስ ስጦታን በተግባር ለማዋል

ጌታ ወንጌልን ሲሰብክ ልዩ ልዩ በሽተኞችን ፈውሷል፤ እንዲሁም ሐዋርያት በሽተኞችን በእግዚአብሔር ኃይል በመጠቀም ፈውሰዋል። ለበሽተኛ ስንጸልይ እግዚአብሔር የፈውስ ስጦታን ሊሰጠን ይችላል።

የፈውስ ስጦታን በተግባር ላይ ከማዋልህ በፊት የሕመሙን መንስኤ ለማወቅ ጸልይ። ሕመሙ ከአካል ችግር፥ በኃጢአት ምክንያት፥ በክፉ መናፍስት በመያዝ፥ ወይም እግዚአብሔር ሊከብርበት ስለፈለገ

የፈቀደው ሊሆን ይችላል። ሕመሙ በኃጢአት ምክንያት ከሆነ በሽተኛውን ከሚያውቃቸው ኃጢአት ንስሐ እንዲገባ ጠይቀው። እንዲሁም ይቅር እንዲል አሳስበው። ሕመሙ ከርኩስ መንፈስ ከሆነ በእግዚአብሔር ቃልና በኢየሱስ ስም እንዲለቅ እዘዘው (የሐዋ. 16፡16–18)። ሕመሙ የአካል ችግር ከሆነም በኢየሱስ ስም ጸልይለት (የሐዋ. 3፡6–8)።

ለበሽተኛው በዚህ መንገድ ከጸለይህለት በኋላ በእግዚአብሔር ቃል፥ በምክርና በማደፋፈር እግዚአብሔርን በሁሉ ነገር እንዲያመሰግንና ለእርሱ ክብር እንዲሰጥ እርዳው (1ኛ ተሰ. 5፡18)። በሽተኛው ተጸልዮለት ከተፈወሰ ጌታ ኢየሱስ ለምጻሞች ሲድኑ ሄዳችሁ እራሳችሁን ለካህናት አሳዩ እንዳለ፤ ለአንዳንድ በሽታዎች ፈውስ ትክክለኛነት ሐኪም ዘንድ ሄዶ ማረጋገጥ ጠቃሚ የሚሆንበት ጊዜ አለ።

<u>ማሳሰቢያ</u> ከጸሎት በኋላ ፈውስ ባይመጣም (ማቴ. 9፡28–29) ለፈውስ በእምነት ጸልየሃልና የተቀረውን ለእግዚአብሔር ጊዜ ተወው፤ ከታገሥህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ፈውስ ወዲያውኑ ወይም እያደር ይመጣል ሉቃስ 17፡15። ከጳውሎስ ጋር ሐኪሙ ሉቃስ ይጓዝ እንደነበረ፥ በሕክምናም በሽተኞች ከበሽታቸው ሲድኑ ይችላሉና በሐኪም መጠቀም ኃጢአት አይደለም። እንደዚሁም እግዚአብሔርን በጸሎት ሳይጠይቁ ወደ ሐኪም መሮጥም አስፈላጊ አይደለም። በሽታው በጸሎት ባይፈወስና በሕክምና ባይድን ለሕመሙ መቻል ለበሽተኛው እግዚአብሔር ጸጋውን ይሰጣልና የጳውሎስን ጸልዮ አለመፈወስን፥ ጥሮፊሞስን ታሞ ትቶት እንደሄደ ማስታወስ ይገባናል 2ኛ ቆሮ. 12፡7–10፤ 2ኛ ጢሞ 4፡20 ደግሞም እኮ! እንደ አሳዛር ከተፈወሱና ከዳኑ በኋላ አንድ ቀን መሞት እንዳለ መርሳት የለብንም።

- **የትንቢት መናገር ስጦታን በተግባር ለማዋል**

ሐዋርያት ወንጌልን ይሰብኩ እንደነበር፤ እነ አጋቦስና ሌሎች ነብያት ትንቢት ይናገሩ ነበር (የሐዋ. 11፡27፤ 21፡9፤ 15፡32)።

አንድ ወቅታዊ መልእክትን ከእግዚአብሔር መንፈስ ለመቀበል የምትችልበት ሁኔታ

– በአምልኮ ስብሰባ ላይ ከቅዱሳን ጋር ሆነህ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለመስማት ተጠባበቅ፤ ለምሳሌ ከቃሉ ጥቅስን፥ ሃሳቦችን ልትቀበል ትችላለህ።

- ለብቻህ በእግዚአብሔር መንፈስ ውስጥ ሆነህ በጸሎት ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ወይም ጥናት ጊዜ የሚታዩህ ነገሮች፥ የምትሰማቸው ድምጾች ወይም በልብህ የሚቀመጡ አሳቦችን ወይም በልብ የሚመላለሱ ነገሮችን በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ፈትነህ ልትቀበል ትችላለህ።

መልእክቱ ስለማን እንደሆነ ለይ

ለራስህ፥ ለግለሰብ፥ ለቤተሰብ ለቡድን ለአገር ወይም ለሕዝብ መሆኑን ጌታን ጠይቀህ ተረዳ።

ቃሉን ተናገር

- በጥሞና ስብሰባ ላይ ሆነህ መልእክቱን ካገኘህ፥ ምቹ ጊዜ ከመሪው በመጠየቅ ፈቃድ ስታገኝ ተናገር።
- መልእክቱ የመጣው ለግለሰብ ከሆነ፥ በግል ለመጣለት ሰው ሄደህ ጸልየህ በጥሞና አናግረው።
- ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ከሆነ በቃል ወይም በጽሑፍ አቅርብላቸው።

ማሳሰቢያ

«ነብያት ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ፤ ሌሎችም ይለዩአቸው፤ በዚያ ለሚቀመጥ ለሌላ ግን አንድ ነገር ቢገለጥለት ፊተኛው ዝም ይበል።» የነብያት መናፍስት ለነብያት ስለሚገዙ» ራስህን ለቤተ ክርስቲያን አስገዛ (1ኛ ቆሮ. 14፡29–33)።

በልዩ ልሳን መናገር

የቃሉ ፍች

በልሳን መናገር ተናጋሪው በአእምሮው ተረድቶ ወይም ቀደም ብሎ አውቆት የሚናገረው ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ የግለሰቡን አንደበት በመጠቀም የሚገልጸው ቋንቋ ነው። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ላይ የተናገሩት ደቀ መዛሙርት ባያውቁትም የተናገሩት በታወቁት የዓለም ቋንቋዎች ነበር። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በምዕራፍ 14 ላይ የተናገሩት የታወቁ ቋንቋዎች ሳይሆኑ ልዩ ልሳናት (መንፈሳዊ ቋንቋዎች) ነበሩ።

በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም

<u>የቃሉ ፍች</u>

ከዚህ በፊት በልሳን ስለተነገረው ቋንቋ የሚረዳውና የሚያውቀው ነገር ሳይኖር በመንፈስ ቅዱስ በመነሣሣትና በእምነት ብቻ የልዩ ልሳኑን ትርጉም በሰሚዎች ቋንቋ መናገር ነው። ከጸለየ፥ አንዳንድ ጊዜ ሰራሱ በልዩ ልሳን ለሚናገረው ትርጉሙ ሊሰጠው ይችላል 1ኛ ቆሮ. 14፡13።

የልዩ ዓይነት ልሳኖች ጠቃሚነት

- በጴንጤቆስጤ ቀን ለአዳማጮቻቸው በሚገባቸው ቋንቋ ራሳቸው ግን ቀድሞ ባላወቁት ልሳኖች መናገራቸው መንፈስ ቅዱስ ለመውረዱ ለአማኞቹ/ ለደቀ መዛሙርት/ ምልክት ነበር (የሐዋ. 1፡5፥ 2፡1-4። 14-33)።

- በኢየሩሳሌም በስግደት ለነበሩ አይሁድችና ከየአገሩ ለመጡ ሌሎችም ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል በራሳቸው ቋንቋ እንዲሰሙ አደረገ (የሐዋ. 2፡6-11)

- የቆሮንቶስ ዓይነቱ በልሳን መናገር ባይተረጎምም ለአምልኮና በምስጋና ለእግዚአብሔር ለመናገር ይጠቅማል (1ኛ ቆሮ. 14፡2፥ 4፥ 14) እንዲሁም ለግል መታነጽ ይውላል (1ኛ ቆሮ. 14፡4)።

- የልዩ ዓይነት ልሳን ተርጓሚ ካለ ቤተ ክርስቲያንን ያንፃል፤ ሆኖም በሥርዓትና ቢበዛ እስከ 3 ሰዎች ተራ በተራ ከተናገሩ ነው 1ኛ ቆሮ. 14፡26-27

- ላላመኑት ምልክት ይሆናል 1ኛ ቆሮ. 14፡22

የልዩ ዓይነት ልሳናት በማን ይሰጣሉ?

የልዩ ዓይነት ልሳናት ለጥቅም በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ ሲሆን፤ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ውጭ በልሳን መናገር ይቻላል። ይኸውም የመንፈስ ቅዱስን ስጦታን በማስመሰል ሊሰጥ ይችላል። ለምሳሌ ባለዛሮች በልዩ ልሳን በርኩስ መንፈስ ተይዘው ይናገራሉ (ማቴ. 4፡9፤ የሐዋ. 16፡6-17) እንዲሁም በሥጋ ምኞትና ግፊት ተነሣሥተው ከሰው በመኮረጅ በልሳን መናገር ይቻላል (1ኛ ዮሐ. 2፡15-16)።

በጴንጠቆስጤ ቀን በተሰጠው ልሳንና በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበሩት ልሳኖች ልዩነት

- በጴንጤቆስጤ ቀን ሁሉም ደቀ መዛሙርት በሌላ ልሳናት ተናገሩ (የሐዋ. 2፡4)። በቆሮንቶስ አንዳንዶች ብቻ ተናገሩ (1ኛ ቆሮ. 12፡30)።
- በጴንጤቆስጤ ቀን ሰው ሁሉ ተረዳቸው (የሐዋ. 2፡6)፤ በቆሮንቶስ ማንም አልተረዳቸውም (1ኛ ቆሮ. 14፡2)።
- በጴንጤቆስጤ ቀን ለሰዎች ተናገሩ (የሐዋ. 2፡6) በቆሮንቶስ ግን ለእግዚአብሔር ተናገሩ (1ኛ ቆሮ. 14፡2፥ 9)።
- በጴንጤቆስጤ ቀን ተርጓሚ አላስፈለገም የሐዋ. 2፡6 በቆሮንቶስ ግን ተርጓሚ አስፈለገ (1ኛ ቆሮ. 14፡23-28)።
- በጴንጤቆስጤ ቀን ምልክቱ ለአማኞችና ላላመኑም ነበር የሐዋ. 2፡7-11፤ 2፡23 በቆሮንቶስ ግን ላላመኑት ነበር (1ኛ ቆሮ. 14፡22)።
- በጴንጤቆስጤ ቀን ያላመኑ ሰዎች ተደነቁ፤ የእግዚአብሔርንም ኃይል ስላዩ ብዙዎች እግዚአብሔርን ፈሩ የሐዋ. 2፡7-8።

አማኞች ሁሉ በልዩ ልሳናት ይናገራሉ ወይ?

በዚህ ጥያቄ ላይ በቤተ ክርስቲያናት ዙሪያ ሦስት አመለካከቶች አሉ፤ አንደኛው በማር. 16፡7፤ 1ኛ ቆሮ. 14፡5፤ የሐዋ. 2፡4፤ 8፡17፥ 10፡45-46፥ 19፡6-7 የተጻፉትን በመጥቀስ አማኞች መንፈስ ቅዱስን ሲሞሉ ልሳን ለሚፈልግ ሁሉ ይሰጣል የሚል ነው፤ ሁለተኛው አስተሳሰብ በ1ኛ ቆሮ. 13፡8-10 የተጻፉትን በመጥቀስ ፍጹም የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ተጽፎ ካለቀ በኋላ ልሳን አቁሟል የሚል ሲሆን፥ ሦስተኛው አመለካከት ያላቸው ግን ልሳን መንፈስ ቅዱስ ወዶ የሚሰጠው ስጦታ ስለሆነ ሁሉ አማኝ ስለፈለገ ብቻ በልሳን አይናገርም። ሁሉም ግን አንዱን መንፈስ አግኝቷል በማለት (ዮሐ. 7፡39፤ የሐዋ. 2፡38፤ 1፡5) 1ኛ ቆሮ. 12፡4-13፤ ሮሜ 8፡9፤ ገላ. 3፡5፤ ቲቶ 3፡4-7፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡20ን ይጠቅሳሉ፤ ስለሆነም እያንዳንዱ አማኝ በመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር መንፈስ ቅዱስ እንደመራው ለጥያቄው መልስ ሊሰጥበት ይገባል፤ የደራሲውን አመለካከት ለማወቅ ከተፈለገ ግን ያለው አቋም የሦስተኛውን አመለካከት የሚደግፍ ነው።

የልዩ ልሳናት ስጦታዎችን በሥራ ላይ ለማዋል

- የግል ልሳናት ለእግዚአብሔር ብቻ የሚነገሩ ናቸው።
  - በግል ጌታን ለማመስገንና ለማምለክ መሻት ቢኖር ራስን ለማነጽ ይውላል፤
- በጉባኤ የሚነገረው ልዩ ልሳን ግን ለሕዝቡ የሚነገር ነው፤ ያውም በልሳን የሚናገር ቢኖር ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው በየተራቸው ሲናገሩ ነው። ለሕዝቡ መታነጽ የሚውለው ግን ሲተረጎም ነው።
  - ትርጉሙ ቃል በቃል ላይሆን ይችላል፤ ልሳኑ ከተነገረ በኋላ መልእክቱ ሊተረጎም ይችላል። «የሚተረጎመው ባይኖር ግን በማኅበር መካከል ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር» (1ኛ ቆሮ. 14፡26-28)።

<u>እናስተውል</u>፡- የማይተረጎም ልዩ ልሳን በጩኸት በቤተ ክርስቲያን እንዲነገር የምናደፋፍር (1ኛ ቆሮ. 14፡19፥23) ወይም ጭራሽኑ ግለሰቡ ለራሱና ለእግዚአብሔር እንዳይናገር የምንከለክል (1ኛ ቆሮ. 14፡2፥39) መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ እንዳለንና እንደሌለን ለይተን እናድርገው። እንዲሁም እዚህ ላይ ደግሜ ወገኖቼን ላሳስብ የምፈልገው፤ በጉባኤ ርዕስ ተሰጥቶ በሚጸለይበት ጊዜ ሁሉም ለየራሱ በግል እንዲጸልዩ ማደፋፈር ብቻ ሳይሆን ጉባኤው በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ጸላይነት እየተደማመጠ መጸለይም አስፈላጊ እንደሆነ በሐዋርያት ሥራ ምዕ. 4 ቁጥር 23 እስከ 31 የተጻፈውን በማንበብ እንድንገነዘብና በሥራ እንድንተረጉም ነው። በጉባኤ የሚደረግ የአንድ ምእመን ጸሎት ደግሞ ባይንዛዛና በርዕሶች ላይ ቢያተኩር ይመረጣል።

በአጠቃላይ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በሥራ ላይ ስለማዋል

የፀጋ ስጦታዎች ለምእመናን መታነጽና ለወንጌል ሥርጭት መዋል የተሰጡ ናቸው (1ኛ ቆሮ. 14፤ የሐዋ. 1፡8፤ ማር. 16፡15-20)

የማነጽ ስጦታዎች፥

- ስጦታዎች የሚሰጡት ለቤተ ክርስቲያን ሆኖ፥ ለእያንዳንዱ የሚሰጡት ለአባላት ጉባኤ ጥቅም ለራስም መታነጽ ነው (1ኛ ቆሮ. 14፡3፥ 12፥ 16፥ 26)።

- እያንዳንዱ ምእመን ጌታን ባመነበት ቀን መንፈስ ቅዱስን ተቀብሏል (ሮሜ 8፡9፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡3፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡20)።

- እያንዳንዱ ምእመን መንፈሳዊ ስጦታዎችን በሥራ ላይ ማዋል ይችላል (1ኛ ቆሮ. 12፡7፥ 11)።

- እያንዳንዱ ምእመን መንፈስ ቅዱስን በመቀበሉ አንድ ስጦታም ቢሆን ሊኖረው ይችላልና የክርስቶስን አካል ለማነጽ በስጦታው መጠቀም አለበት (1ኛ ቆሮ. 14፡3፥ 6፥ 12፥ 26፤ 2ኛ ጢሞ 1፡6–7)።

ለወንጌል ሥርጭት የሚጠቅሙ ስጦታዎች

– «መንፈስ ቅዱስ በወረደባችሁ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ» (የሐዋ. 1፡8)።

– «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፥ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፥ ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል። ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል። በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፥ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፥ እባቦችን ይይዛሉ፥ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፥ እጃቸውንም በድውዮች ላይ ይጭናሉ፤ እነርሱም ይድናሉ... እነርሱም ወጥተው በየስፍራው ሰበኩ፥ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር፥ በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያፀና ነበር» (ማር. 16፡15–20)።

<u>ማሳሰቢያ</u> የጸጋ ስጦታዎችን አገልጋይ በባለቤትነት ይዞ በዘፈቀደ የሚሠራባቸው የግል ንብረቶቹ አይደሉም። መንፈስ ቅዱስ ቦታውን፥ ጊዜውንና ሁኔታውን ሁሉ እንደወደደና እንደፈቀደ ለአገልጋዩ የሚገልጥባቸው ናቸው እንጂ (2ኛ ነገሥ. 4፡27)፤ በመሆኑም እገሌ ወይም እገሊት ይህ ስጦታ አላቸው በሚል ለአንዴና ለሁሉ ጊዜ መመደብ አስፈላጊ አይደለም።

<u>ሐ) የጸጋ ስጦታዎች መፈተኛዎች</u>

- በእግዚአብሔር ቃል ፈትን፡– ስጦታ ተብሎ የሚነገረውንና የሚደረገውን ከእግዚአብሔር ቃል መቃረኑን ወይም መስማማቱን አረጋግጥ (ቆላ. 3፡16)።

- በሰሚዎች ላይ ሰላምን ያመጡ እንደሆነ፥ ወይም በኃጢአት መወቀስንና ንስሐ መግባትን፥ ወይም ትቀሰፋላችሁ በማለት

ፍርሐትን ብቻ የሚለቁ መሆናቸውን ለይ (1ኛ ቆሮ. 14፡33)። ሰዎችን ወደ ጌታ ይስባል ወይስ ወደ ተናጋሪው? በሚልም መፈተን ትችላለህ። በሌላ በኩልም ያልተጨበጠ ተስፋ በመስጠት ሰዎችን ይመራል ወይ? በሚል ፈትን እንጂ የመንፈስ ቅዱስን ወይም የጌታ ኢየሱስ ስምን አገልጋዩ ስለጠቀሰ ብቻ ልክ ነው ብለህ አትቀበል።

- ከስጦታው በስተጀርባ ያለው መንፈስ የቱ ነው? ከእግዚአብሔር፥ ከሥጋ ወይስ ከሰይጣን ብለህ በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በጸሎትም አረጋግጥ 1ኛ ቆሮ. 12፡10፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡8-11፤ የሐዋ. 16፡18።

- ትንቢቱ ወይም የፈውሱ ቃል ተፈፃሚነት አለው ወይ? ዘዳ. 18፡22 (ይህንንም ማስታወሻ በመጻፍ መፈጸሙንና አለመፈጸሙን ማረጋገጥ ይቻላል ወይም ለአንዳንድ ሕመሞች ፈውስ እንደተገኘ ወይም እንዳልተገኘ በሐኪም ማስረጃ ማረጋገጥ ይቻላል)

- በእግዚአብሔር መንፈስ ገላጭነት ተማመን (ዮሐ. 14፡26፥ 16፡13)።

- በፍሬው ታውቀዋለህ። ስጦታው ያለው አማኝ ራሱ ኃጢአትን ይለማመዳል ወይ? (ማቴ. 7፡15-19)።

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- በስጦታዎች ትርጉምና ስለስጦታዎች አጠቃቀም አማኞች ብንለያይም የመንፈስን አንድነት እንጠብቅ-ለምን? ቢሉ፡-

- ስጦታውን የሰጠው አንዱ መንፈስ፥ አንዱ ጌታ፥ አንዱ እግዚአብሔር እንደፈቀደ ስለሆነ ኤፌ. 1፡4፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡4-6፥ 11

- የእግዚአብሔርን ፍጥረት በሙሉ ብንመለከት ልዩ ልዩ ስለሆኑ ሁሉም ግን አስፈላጊ ሆነው ስለተፈጠሩ ዘፍ. ምዕ 1።

- ሰው እንኳን አንድ ቢመስልም አንዱ ከሌላው በመልክ፥ በቁመት፥ በውፍረት በቅጥነት፥ በጾታ፥ በችሎታና በመሳሰሉት የሚለያይበት ነገሮች አሉትና፤

- ወፎችና አበቦችም የመሳሰሉትም ፍጥረታት ልዩ ልዩ መልክና ሥራ፥ ችሎታ አላቸውና ቢለያዩም ይጠቅማሉና በስጦታ ልዩነታችንን በጸጋ እንቀበል ሮሜ 15፡7

አንድነታችንንና ፍቅራችንን እንድንጠብቅ ታዘናልና (ኤፌ. 4፡3፤ ዮሐ. 15፡17፤ ፊልጵ. 2፡1-5)።

ስለ አንድነታችን ጌታ ኢየሱስ ጸልዮልናልና (ዮሐ. 17፡20-21)።

ፍቅርና ኅብረት ሲኖረን የሚድኑት ወደ ጌታ ኢየሱስ በእምነት ይመጣሉና (ዮሐ. 13፡35፤ የሐዋ. 2፡46-47)።

መ) <u>የመንፈስ ፍሬና መንፈሳዊነት (ገላ. 5፡22)</u>

የመንፈስ ፍሬ፥ ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት እምነት፥ የዋህነት፥ ራስን መግዛት በአንድ ምእመን ወይም ቤተ ክርስቲያን አባላት መታየት አማራጭ የሌለው ነው። የአንድ አማኝ መንፈሳዊነት የሚለካውም በዚህ በመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው። በ1ኛ ቆሮ. 13 ላይ በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብንናገር፤ ትንቢት ቢኖረን፤ የእግዚአብሔር ነገር ምስጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ብናውቅ፤ ተራሮችንም እስከናፈልስ ድረስ እምነት ቢኖረን፤ ድሆችን ለመመገብ ያለንን ሁሉ ብናካፍል፤ ለእምነታችን ስንል ሥጋችንን ለእሳት እንኳ አሳልፈን ብንሰጥ፤ ፍቅር ግን ከሌለን ምንም እንደማይጠቅመን እቅጩን ይነግረናል። ለምን ቢሉ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ እግዚአብሔርንም እወዳለሁ የሚል ወንድምኑን ወይም እህቱን መውደድ አለበት። ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም» ይላል። እምነት፥ ተስፋ፥ ፍቅር፥ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው (1ኛ ዮሐ. 4፡7-21)።

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ግምት የሰጠነው ለልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች መሆኑና የሚ ጎድሉትን የጸጋ ስጦታዎች በበለጠ መፈለጋችን የሚደገፍ ቢሆንም የመንፈስ ፍሬ በሕይወታችን እንዲገለጥ፥ ክርስቶስን ወደ መምሰል እንድንደርስ ልዩ ትጋትና መሻት ያስፈልገናል።

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የፈሰሱባት ቤተ ክርስቲያን ነበረች። የጸጋ ስጦታ አልጎደለባቸውም ነበር (1ኛ ቆሮ. 1፡4-7) ዳሩ ግን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በመካከላቸው አልነበረም፤ እንዲያውም ቅናትና ክርክር ነበረባቸው፤ ተከፋፍለውና ተለያይተው ነበር፤ (1ኛ ቆሮ. 1፡10-12፤ 1ኛ ቆሮ. 3፡3-4) በዚህ ምክንያት መንፈሳዊ ስላልነበሩ ሕፃናትና ሥጋውያን ተብለዋል። ልዩ ልዩ ጋጢአት በመሥራት ንስሐ ሳይገቡ መንፈሳዊ ነን ብለው ኮርተው እኔ ከሌላው እሻላለሁ እያሉ ተቀምጠው ነበር፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን እናንተ ሥጋውያን ናችሁ አላቸው።

መንፈሳዊነት በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር የሆነ ውስጣዊ ሰው ነው። ቅድስና፤ የቅድስና ኑሮ፥ እግዚአብሔርን መምሰል፥ ከእግዚአብሔር ጋር አካሄድን ማሳመር፥ የክርስቶስ ደቀ መዝሙርነት ሁሉ ከመንፈሳዊ ሕይወት ጋር የተያያዙ ናቸው። መንፈሳዊነት ክርስቶስን ማዕከላዊ ያደረገ ሕይወት ነው። እኛ አማኞች ሁልጊዜም በክርስቶስ ውስጥ እንዳለንም ማመን ብቻ ሳይሆን በእርሱ መኖር

አለብን። የጌታ ኢየሱስ ሕይወት በእኛ በአማኞች እያደገ እንዲሄድ መፍቀድ አለብን። ምክንያቱም እኛ ሳንሆን እርሱ በእኛ እንዲታይና እኛ እርሱን እንድንመስል ነው። ሮሜ 8፡29 ይህም ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ጸጋ በእኛ ውስጥ እንዲሠራ መፍቀድ አለብን። ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ፊት ሆነን እንደምንኖር በጥብቅ ማወቅ አለብን (2ኛ ዜና 29፡11)። በኃጢአት መንፈስ ቅዱስን ሳናሳዝነውና ስጦታዎችን በመናቅ ወይም ቸል በማለት የመንፈስ ቅዱስን እሳት ሳናጠፋ ባለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ እየተሞላን መቀጠል አለብን (1ኛ ተሰ. 5፡19-20፤ ኤፌ. 4፡18-19፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡14፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡6-7)። እግዚአብሔርንም በእውነትና በመንፈስ ማምለክ አለብን (ዮሐ. 4፡23-24)። ይህም የዘወትር ሕይወታችን ነፀብራቅ መሆን አለበት (ሮሜ 12፡1፥ 14፡6-8፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡31)

አስተውሉ፥ በመንፈስ ፍሬ ውስጥ የተጠቃለሉትን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የዋህነት፥ ራስን መግዛት ሁሉ በሕይወታችን ልንለማመዳቸው የሚያስፈልጉ የመንፈሳዊነታችን መለኪያ ናቸውና ምእመናን በትጋት እንከታተላቸው።

ማጠቃለያ

የአገልግሎት ስጦታዎች፥ የጸጋ ስጦታዎችና የመንፈስ ፍሬ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ተጣጥመውና ተዋህደው ሲገለጹና እያንዳንዱ አማኝ የተመደበለትን ተግባር ለሌሎች አገልጋዮች ቀኝ እጁን በአገልግሎት ከመስጠት ጋር ሲያከናውን አካል በሙሉ ያድጋል፥ በፍቅርም ይታነፃል። እውነትንም በፍቅር እየተናገረ ራስ የሆነውን ክርስቶስን ለመምሰል በሁሉ ነገር ያድጋል (ኤፌ. 4፡15-16፤ ገላ. 2፡8-10)። እያንዳንዱ አማኝ በጥሪውና ስጦታው ከማገልገሉ በፊት ደግሞ የአገልጋይነት ምንነትን ማወቅ ይኖርበታል። አገልጋይ ማለት ራሱን ለክርስቶስና ለሕዝቡ ሰጥቶ ዝቅ ብሎ የሚያገለግል ነው (1ኛ ጴጥ. 5፡1-6፤ ሮሜ 12፡1-2)፤ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ላሉ የሚያስፈልጋቸውን መንፈሳዊንና አካላዊ ምግብ በየጊዜው የሚያቀርብ ነው (የሐዋ. 6፡3-4፤ ሉቃስ 12፡41-43)፤ አገልጋይ በማዕድ የተቀመጡትን ከራሱ እንደሚበልጡ አድርጎ የሚያገለግል ነው። (ሉቃስ 22፡26-27)። ብዙውን ጊዜ በመድረክ ላይ የምናገለግል አገልጋዮች በቤተ ክርስቲያን ተቀምጠው የምናገለግላቸውን የሚገባቸውን ክብር ሳንሰጥ እኛ ትልቅ ነን፤ ሰጪ ነን ብለን ካሰብን የአገልግሎት ትርጉም አልገባንም ማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና መምህር ሲሆን በደቀ መዛሙርቱ መካከል እንደ አገልጋይ ራሱን ቆጥሮ እስከ እግሮች ማጠብ ድረስ አገለገላቸውና እናንተም እርስ በርሳችሁ ሌላውን

በዚህ መንገድ አገልግሎ አላቸው (ዮሐ. 13፡12-17) በተጨማሪም አገልጋዮች የራሳቸንን አገልግሎት ትተን ስለ ሌላው አገልግሎት ጣልቃ መግባት እንፈልጋለን ይህ የሚያገባን አይደለምና የራሳችንን አገልግሎት እንፈጽም (ዮሐ. 21፡23፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡5)፤ የሌላውን አገልግሎት መሻማትም የለብንም በራሳችን ላይ ፍርድን እንዳናመጣ (1ኛ ሳሙ. 13፡8-14፤ 2ኛ ዜና 26፡16-20)።

ስለሆነም በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በየዲኖሚኔሽኑ ጤናማ እድገት እንዲኖር ሁላችንም በተሰጠን ስጦታዎች ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መስዋዕትን እናቀርብ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት በመሆን መንፈሳዊ ቤት ሆነን ለመሠራት እንትጋ (1ኛ ጴጥ. 2፡5)።

8. የቤተ ክርስቲያን ዓላማና ተልእኮ

ዛሬ በአንዳንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያሉ አንዳንድ አገልጋዮች ቀደም ብሎ ከነበሩበት ዋናዎቻቸው ያዩት እንዳለ እንዲቀጥል የሚያደርጉ ወይም አዲስ ነገር ባዩ ቁጥር ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ጉዳዩን ሳያመሳክሩና ሳይመረምሩ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ይሞክራሉ። ስለሆነም ያለውን ለመጠበቅ ወይም አዲስ ነገር ባዩ ቁጥር ያንን ለማድረግ ከመቻኮል የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዓላማና ተልእኮ ምን እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሊያጠኑና ያንን ተግባራዊ ማድረግ ይጠቅማቸዋል።

- አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያላት ዓላማና ተልእኮ በሚከተሉት ሊካተት ይችላል።
- አንዲት አጥብያ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ኢየሱስና እርስ በርሷም አንድ የሆነች መሆን አለባት (1ኛ ቆሮ. 12፡12-13፤ ኤፌ.4፡3-6)።
- ከዓለም ርኩሰት ወጥታ የተቀደሰች መሆን ይኖርባታል (1ኛ. ጴጥ. 2፡9-10፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡14-18)።
- የሰውን ቀለም፥ ዕድሜ፥ ጾታ፥ ጎሣ፥ የፖለቲካ አመለካከት ወዘተ፥ አይታ ማዕቀብ ሣታደርግ ለሁሉም ክፍት ልትሆን ይገባል (ገላ. 3፡26-28)።
- በስድሳ ስድስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተጻፈውን የእግዚአብሔር ቃል ስልጣንና ትምህርት አምና የተቀበለች መሆን አለባት (የሐዋ. 2፡42፤ ኤፌ. 2፡20-21፤ 2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡20-21)።

- የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ የምትሰብክና የምታስተምር ልትሆን ይገባል (ማር. 16፡15)። ከቃሉ ጋር ለችግረኞች ለአካላቸው እርዳታ ልታደርግ ያሻል (ገላ. 2፡10፤ ኤፌ. 6፡9–10)።

- ቅዱስ ቁርባንና ጥምቀትን የምትፈጽም የምታስፈጽም ጌታ ኢየሱስን የምታመልክና የምትጸም በጸሎትም የምትተጋ መሆን አለባት (ማቴ. 28፡19–20፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡23–26፤ የሐዋ. 13፡2–3፤ የሐዋ. 2፡42)።

- የምሥራቹን ቃል ላልሰሙት ሕዝብ ወንጌላውያንን መላክ፤ እንዲሁም አባላቱን በያሉበትና መንፈስ ቅዱስ በሚሰጣት ስልት ወንጌልን ላልሰሙ እንዲመሰክሩ በማበራታት የምታገለግል መሆን አለባት፤ እንዲሁም ለወንጌል ሥራ ገንዘብ መስጠት ይጠበቅባታል (የሐዋ. 13፡1–3፤ የሐዋ. 8፡4)።

9. ቤተ ክርስቲያን በየቦታው ለመጀመር የሚያስፈልጉ ዋና ነገሮች

በአሁኑ ጊዜ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በወንጌል ስርጭት ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ወንጌልን ካሰራጩ በኋላ አጥብያ ቤተ ክርስቲያናትን የመመሥረት ነገር ስለማይቀር ከዚህ ተልዕኮ ይጠቅማል በሚል የሚከተሉት ጠቋሚ ሀሳቦች ቀርበዋል።

የቤተ ክርስቲያን ተካዮች ባሕርያት

- የጸሎት ሰው መሆን፥
- ለነፍሳት ፍቅር ያለው፥
- የአገልግሎት ጥሪ ያለው፥
- የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ያገኘ፥
- ባለራእይነትና ቢያንስ የመሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስን እውቀት ያገኘ፥
- ለቤተ ክርስቲያን ተገዥ የሆነና የመሳሰለ መሆን ይኖርበታል።

የቤተ ክርስቲያን ተከላ ተግባራት

- አካባቢን ማጥናትና መረጃ ማሰባሰብ፥

- ስለ አካባቢው መጻለይ፥
- አገልጋዮችን መመልመልና ማሠልጠን፥
- አስፈላጊ ገንዘብና ማቴሪያል ማሰባሰብ፥
- የወንጌል ስርጭት ስልትን መንደፍ፥
- ወንጌልን መስበክ
- የዳኑትን መከታተልና፥ ማሳደግና የመሳሰሉትን ያካትታሉ። በነዚህ የቤተ ክርስቲያን ተካዮች ባሕርያትና ተግባራት ተነሥቶ የሚከተሉትን ማድረግ ያስፈልጋል፤
- <u>ቤተ ክርስቲያን ለመትከል የሚያስቡ ሁሉ፥ ጊዜያቸውን በጸሎት ማሳለፍ፥ ይኖርባቸዋል</u>።

የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ጌታን ስታመልክና ስትጾም ነው በርናባስንና ጳውሎስን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ ሲል መንፈስ ቅዱስ የተናገራት ያለጸም፥ ጸሎት ሰይጣን በሥሩ ያሉትን ሕዝቦች አይለቅም። የሐዋ. 13፡1-3 የርሱን መንግሥት ለመበዝበዝ እርሱን ማሰር ያስፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን የምትወለደው በጸሎት ስታምጥ ነው። ስለዚህ መላው ምእመንን በግል፥ በቤተሰብ፥ በሰፈር፥ በቤተ ክርስቲያን፥ በጸሎት ሽማግሌዎች ማሳለፍ ይገባቸዋል (ኤፌ. 6፡18-20፤ ማቴ. 17፡21፤ ማቴ. 12፡29፤ ኢሳ. 66፡8)።

- ቤተ <u>ክርስቲያንን የሚተክሉ ብዙ ዓይነት የወንጌል ሥርጭት ስልቶችን አውቀው ሊጠቀሙባቸው ይገባል</u>።

የወንጌል ስርጭት ስልቱ አንድ አይደለም ብዙ ነው፤ ስለሆነም ከሌሎች ልምድ በመማር እንዲሁም ምእመናን በማማከር ከሁሉ በላይ ጌታ በሚያሳያቸው ልዩ ልዩ ምሪቶች ብዙ ስልቶችን መጠቀም ሲሆን ለምሳሌ የኢየሱስ ፊልምን በማሳየት፥ መንፈሳዊ መልእክት በቪዲዮ በማሳየት፥ ከተማ ወይም መንደር አቀፍ ወንጌልን ሥርጭትን በማድረግ፥ ትራክትንና የመሳሰሉትን ጽሑፎች በማደልና በመመስከር፥ ለበሽተኞች በይፋ በመጸለይ፥ ለሕፃናትና ለወጣቶች መንፈሳዊ ቲያትር በማቅረብ ወይም በስፖርት አሳትፎ የደህንነት ወንጌልን በመስበክና በመሳሰለው በመጠቀም እንዲሁም ምእመናን በጥንድ እያደረጉ ቤት-ለቤት በመሄድ ወንጌልን በማሰራጨት ብዙ ምእመናን ማሳተፍ ይቻላል፤ ሆኖም ሌሎች ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የጌታ ኢየሱስን ስም በሰበኩበትና በሚሰብኩበት አካባቢ በመሄድ ሌላ መሠረት ለመመሥረት መነሣት ተገቢ ስላልሆነ ቤተ ክርስቲያናት

ሊጠነቀቁ ይገባል (ሮሜ 15፡18-28)። እንዲሁም ስልቶቹ ታይተው ብዙ ውጤት ካላመጡ በነዚያ ላይ ሙጭጭ ሳይሉ ዘዴዎችን እንደ አስፈላጊነቱ መቀየር መልካም ነው።

- ጥርት ላለና ለታወቀ የቤተ ክርስቲያን ዶክትሪን ራስን ሰጥቶ ማስተማር አስፈላጊ ነው።

አዳዲስ ሰዎች የወንጌል አሠራጩን የእምነት አቋም ለማወቅ ይፈልጋሉና ተከታታይ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ነው። የእምነት አቋም በግልጽ በማይሰበክበት ቦታ ሰዎች ጌታ ኢየሱስን በውል አውቀው ለመከተል ግራ ይጋባሉ፤ ስለዚህ ለወንጌል ስርጭትና ለቤተ ክርስቲያን ምሥረታ አባላት ሲላኩ የሚያምኑትን ጥርት አድርገው እንዲያውቁና በበጎ ሕሊና መልስ ለመስጠት የተዘጋጁ መሆን ይኖርባቸዋል (1ኛ ጴጥ. 3፡15-16)።

- የሚላኩ አገልጋዮች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ለመጀመር የሚችሉና የማያሳፍርና ታማኝ አገልጋዮች መሆን ይኖርባቸዋል። በሕብረተሰቡም ታማኒነትን ማግኘታቸው አስፈላጊ ነው (2ኛ ጢሞ. 2፡15)።

ያንን ታማኒነት ለማግኘት ወደ ጎብረተሰቡ በመሠረተ ትምህርትና በቀለም ትምህርት በማስተማር፤ በሕፃናትና ቤተሰብ እርዳታ አገልግሎት፥ በንፁህ ሙያ አቅርቦትና በመሳሰለው መቅረብ ይቻላል፤ ይህም ሲሆን የልማቱ ሥራን ለወንጌል ስርጭቱ እንደአጋዥ እንጂ ልማት ዋናው ዓላማ ሆኖ እንዳይወሰድ ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

- አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመር አጥባቂ ሃይማኖተኞች ያልሆኑትን ክፍሎች ለይቶ በማወቅ ለእነርሱ መመስከርን ይጠይቃል።

አጥባቂ ሃይማኖተኞች ባሉበት አካባቢ ወንጌልን ለማሠራጨት ብዙ ጊዜ ከመውሰዱም ሌላ፤ ወደ ሌሎች ስፍራ ወንጌልን ለማሰራጨት ያለውን ዕድል ሊያመክነው ይችላል፤ ስለዚህ ስር የሰደደ የሃይማኖት ክፍል ወደ ሌለበት አዲስ ስፍራ ወይም የቤት ሥራ ተጀምሮ ገና ባለቀበት ቦታ በቅድሚያ የወንጌል ስርጭትን ማድረግ ጠቃሚ ነው፤ ይህም ስለተባለ በእርግጥ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ወደነዚያም አክራሪ ክፍሎች እንዲኬድ የሚያዝ ከሆነ የመንፈስን ትእዛዝ ተከትሎ ማድረግ የተሻለ ነው።

- በአዲስ ስፍራ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመር ቀደም ብሎ በስፍራው ባሉት ጥቂት አባላት መጠቀም ይረዳል።

በአዲስ ስፍራ ቤተ ክርስቲያንን ለመትከል በመጀመሪያ በዚያ ወንጌል ሊሠራጭ ባስፈለገበት ባሉ አንድ ቤተሰብ ወይም ሁለት አባላት ጅምሮ እያስፋፉ መሄድ ጠቃሚነቱ ታይቷል፤ ስለሆነም ወንጌላዊ በመላክም ሆነ እነዚያን አባላት በሚያስፈልገው በመርዳት የወንጌል ሥራ ቢጀመር በአጭር ጊዜ ውስጥ ተስፋፍቶ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል ይቻላል። እንዲሁም ቋንቋና ባሕልን በወንጌል ስርጭቱና በአምልኮ ሥርአት ውስጥ ማዋሃድ ጠቃሚነት ይኖረዋል። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከተተከለም በኋላ ሳያድጉና ሳይደራጁ ቶሎ መተው አደጋ አለው።

- <u>የተሳካላቸው፥ ቤተ ክርስቲያንን በየቦታው የሚጀምሩ አገልጋዮች አዲስ አማኞችን በወንጌል ሥርጭታቸው ያካፍላሉ።</u>

ለአዳዲስ አማኞች በወንጌል ሥርጭት በቂ ስልጠና ሰጥቶና መመሪያም የሚሆን ጽሑፍ በሚገባ አዘጋጅቶ በመካከላቸው ጠለቅ ያለ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ያለውን መሪ አድርጎ ማሰማራት ጠቃሚነት አለው። ከእነዚህም ብዙዎች ሊያቋርጡ ቢችሉም የተቀሩት መሪ አገልጋይ ደረጃ እንኳ ሊደርሱ ይችላሉ። አዳዲስ ሰዎችን እንዳመኑ ወዲያውኑ አጥምቆ አባሎች ማድረግና በወንጌል ስርጭት ማሳተፍና ጎን ለጎንም በዶክትሪን ነገር ማሰልጠን የሚጠቅም ሲሆን፤ አባል ሳያደርጉ በዶክትሪን ትምህርት ክትትል ለብዙ ጊዜ ማቆየት ተስፋ ቆርጠው እምነታቸውን እንዲጥሉ ያደርጋል፤ ስለሆነም አዳዲስ አማኞች ገና የተነቃቁ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ቆይተው ከማይንቀሳቀሱት አባላት ይልቅ በወንጌል ሥራ ማሳተፍ ከውጤት ይደርሳልና ሊታሰብበት ይገባል፤ ይህም ቢባል ለቤተ ክርስቲያን እድገት ውጤት የሚሰጠውና የሚድኑትን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚጨምረው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ከእርሱ ጋር ቤተ ክርስቲያናት መተባበራቸው ለወንጌል ስርጭት ወሳኝ ነው።

10. በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ እድገትን ማስገኘት ጠቀሜታ ያላቸው አሳቦች

1ኛ ጢሞ. 4፡15

በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ እንቅስቃሴና የተሟላ እድገትን የሚያመጣው የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በዘላለማዊ እቅዱ መሠረት፥ በራሱ ጊዜና ፈቃድ መሆኑ የታወቀ ነው (ዘፍ. 15፡15፤ ገላ. 4፡4፤ የሐዋ. 1፡6–7፤ ዮሐ. 7፡6–9፤ 2፡4፤ 20፡21–22፤ ማቴ. 16፡18፤ ኤፌ. 1፡22–23፤ የሐዋ. 2፡47፤ 8፡26–29፥ 39–40፤ 10፡19፤ 13፡2፤ 16፡6–10)፤ ያም ቢሆን

በመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጸው ፈቃዱ መሠረት የሚከተሉትን መመሪያዎች ምከተል መንፈሳዊ እንቅስቃሴንና ሁለተናዊ እድገት በቤተ ክርስቲያን ያመጣልና እንጠቀምባቸው።

ሀ) <u>እርም የሆነውን በማውጣት ራስን ለእግዚአብሔር መቀደስ ያስፈልጋል።</u>

እግዚአብሔር በመካከላችን እንዲሠራ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ምእመናን ከታወቁ ኃጢአቶች ንስሐ በመግባት እርም የሆነውን ነገር በንስሐ ማስወገድ ያስፈልጋል። በኢያሱ 7፡1-13 መሠረት ከሥርቆት እርም ንስሐ በመግባት በ1ኛ ሳሙ. 2፡12-17፥ 22፤ 4፡10-11 መሠረት እግዚአብሔርን ከመናቅና ከዝሙት ንስሐ በመግባት የእርስ በርስ መዋደድ ጎብረት ማድረግ (በሐዋ. 19፡10፡1-15፤ 1ኛ ተሰ. 4፡1-8፤ ዕብ. 12፡14፤ ያዕ. 3፡14-16) መሠረት በቅንአት፥ በአድመኝነት፥ በመራራነት በመከፋፈል ከመመላለስ ንስሐ መግባት። (ሐዋ. 2፡1፥ 46፤ 4፡24፥ 32፤ 5፡12፤ የሐዋ. 4፡20፤ 5፡32፤ ኢሳ. 6፡8፤ ማር. 7፡6-9)። የእግዚአብሔርን መንፈስ ቅዱስ በማዳመጥና በመታዘዝ ፈንታ በቤተ ክርስቲያን ወግና ሥርዓት ደንብ ከመታሰር ንስሐ መግባት ያስፈልጋል (ዮሐ. 5፡15-17፤ 1ኛ ተሰ. 5፡19)።

ለ) <u>ከእግዚአብሔር ራዕይ ለማግኘት ጸሎት ማድረግና በሚገኘው ምሪት ዓመታዊ እቅድ መዘርጋት አፈጻጸሙን መከታተልና ውጤቱንም መገምገም ያስፈልጋል።</u>

የሐዋ. 1፡14፤ 13፡1-3 በጸሎት አስፈላጊም ሲሆን በጾም የእግዚአብሔርን ፊት በመሻትና የከብሩን መገለጥ መጠባበቅ ኢሳ. 40፡31

ሐ) <u>የሥራ ክፍፍል ማድረግና ለየአገልግሎቱ ተጠሪ መሰየም</u>

በተለይም በሽማግሌዎች፥ በወንጌላዊያን፥ በዲያቆናት፥ በሴቶች፥ በወጣቶች፥ በመዘምራንና ለየኮሜቴው ተጠሪ መሰየም፤ ለምሳሌ ለጸሎት፥ ለቃሉ፥ ለመዝሙር (ለሕጻናት፥ ለመረዳጃ፥ ለሙያማሰልጠኛ፥ ለከተማ አገልግሎት፥ ለትምህርት ቤት፥ ለጽ/ቤትና ለመሳሰለው)

መ) <u>ሰዎችን በስጦታዎቻቸው ማሰማራት</u>

የአገልግሎት ዓይነቶች ዝርዝር በማውጣት ስለ ሥጦታዎች ማስተማር እያንዳንዱ ምእመን ጸልዮ በምን ማገልገል እንደሚፈልግ መልስ እንዲሰጥ በማድረግ ሽማግሌዎች ጸልየው ካረጋገጡ በኋላ አስልጥነው ምእመናንን በስጦታቸው ማሰማራት ነው። 1ኛ ጴጥ. 4፡10-

11፤ ሮሜ 12፡6–8፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡4–10፤ ሉቃስ 5፡10–11፥ 27–28፤ ሉቃስ 6፡12–16፤ 8፡9–10፤ ዮሐ. 20፡21–23 <u>የሽማግሌዎች ዋና ዋና ሥራዎች በአባላት ያለውን የጸጋ ስጦታ ማንቀሳቀስ ስለሆነ</u> በተወሰኑ ጊዜያት በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ በሚፈልጉ አባላት ላይ በእጅ መጫን በውስጣቸው ያለውን የጸጋ ስጦታዎች ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል (2ኛ ጢሞ. 1፡6፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡14–16) እና በስጦታዎችም መጠቀም ለአባላት መታነጽ ይውላል 1ኛ ቆሮ. 14፡26።

ሠ) <u>የመስካሪ ቡድን ማዘጋጀት</u>

ተከታታይ ጥሪ በማቅረብ ፈቃደኞችን በመቀበል፥ አሰልጥኖ ለወንጌል ሥርጭት በቡድን በቡድን በማድረግ ከቡድን መሪ ጋር ማሰማራት (ማቴ. 10፡5–11፤ ማር. 6፡7–13፤ ሉቃስ 9፡1–2)፤ መንፈሳዊ ልምምዳቸውን በወንጌል ስርጭት ያገኙትን ውጤት በቤተ ክርስቲያን እንዲመለከሩ በማድረግ መነቃቃት ያመጣል። ሉቃስ 10፡17፤ የሐዋ. 14፡24–28 ቤተ ክርስቲያን ለሰዎች ነፍስ ብቻ ሳይሆን <u>ለሥጋቸውም በምትችለው ብታደርግ ምስክርነቷ</u> ማረጋገጫ ይኖረዋል ገላ. 6፡9–10፤ ያዕ. 2፡8።

ረ) <u>የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን በአባላት መካከል ማስፋፋት</u>

የግለሰብ፥ የቤተሰብ፥ የሰፈርና የቤተ ክርስቲያን <u>ጸሎትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ማጠናከር</u>፤ ለሰፈርና ለቤተ ክርስቲያኗ ጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች የቡድን መሪዎችንና አስተባባሪዎችን መሰየም ወቅታዊ ነው። <u>የሰንበት ትምህርት ቤቶችን በሰፈርና በቤተ ክርስቲያን ማቋቋምና ማጠናከር</u> ለነዚህም አስተማሪዎችንና አስተባባሪዎችን መለየት ያስፈልጋል።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ማቋቋም</u> ለዚህም ቋሚ አስተባባሪና በትርፍ ጊዜአቸው የሚያገለግሉ ፈቃደኛ መምህራንን ማዘጋጀትና ማሰማራት ነው (በሐዋ. 2፡41–42፤ የሐዋ. 19፡9–10፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡2)። በየእሑዱ የአምልኮ ሰዓት በወቅቱ ችግሮችንና መሠረታዊ የክርስትናን ኑሮ ለማስጨበጥ በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ ተከታታይ ትምህርትን መስጠት ወሳኝ ነው።

ሰ) <u>በየአካባቢው ጸሎት ቤቶችን መክፈት</u>

ወንጌል በአንድ አካባቢ ሲስፋፋ ወይም ምእመናን በበዛበትና ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ራቅ ብለው በሚገኙ ቦታዎች ጸሎት ቤቶችን መክፈት ለሌላ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መወለድ ምክንያት ይሆናልና በየጊዜው ሁኔታዎችን እየገመገሙ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ተከትሎ

ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። በእነዚህ ቦታዎች አገልጋዮችን መመደብ ወሳኝ ነው ቲቶ 1፡5-9፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡2።

ሸ) <u>የእሑድ አምልኮን በተመለከተ</u>

የእግዚአብሔር ቤት የጸሎት ቤት ነው ማቴ. 20፡13። የጸሎትም ትልቁ ክፍል ደግሞ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ነው፤ ስለዚህ ከጸሎቱ ጋር በመዝሙር በአምልኮና በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ምእመኑን ማቅረብ አስፈላጊ ነው፤ የምስጋናው ይዘትም እግዚአብሔርን ስለማንነቱ፥ ስለ ባሕርዩ፥ ስላደረጋቸው፥ ነገሮች እያወቀ ማመስገን ነው፤ የምስጋና ርዕሶች ወይም መዝሙር በእነዚሁ ቢያተኩር ጥሩ ሊሆን ለአንድ አዝማች ብቻ ከሚገባው በላይ ጊዜ አለመውሰድን ይጠይቃል። ስለሆነም ለዚህ አገልግሎት ስጦታ ያላቸው ሰዎች ጉባኤውን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲመሩ ማድረግ ጥሩ ነው። ከዚህ ጋር አያይዞ ጉባኤውን ወደ እግዚአብሔር አሳብ የሚያመጣ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተዘጋጀ የወንጌል መልእክት አብሮ መቅረብ አለበት። ለዚህም ዓይነት የስብከትና የማስተማር አገልግሎት ብቃት ያላቸውን አገልጋዮችንም መመደብ ወሳኝ ነው (መዝ. 107. 1-22፤ ኢሳ. 43፡21፤ መዝ. 100፡4፤ ያዕ. 5፡13፤ 1ኛ ተሰ. 5፡18፤ ራእይ 4፡8፤ መዝ. 92፡1 መዝ. 68፡19፤ ኢያሱ 6፡5፤ መዝ. 56፡3-4፤ 2ኛ ቆሮ. 9፡15፤ 2፡14፤ ቆላ. 3፡16፤ የሐዋ. 16፡25፤ ኤፌ. 5፡18-20፤ 2ኛ ዜና 20፡22፤ መዝ. 22፡3 መዝ. 34፡1፤ 1ኛ ዜና 23፡5፤ ዕብ. 13፡15፤ የሐዋ. 2፡36-42፤ ሉቃስ 4፡16-22፤ መዝ. 145፡3፤ ማቴ. 7፡28-29፤ 1ኛ ቆሮ. 14፡24-25፤ ዮሐ. 4፡23-24፤ የሐዋ. 13፡1-3)።

<u>ማሳሰቢያ</u> በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት የእሑድ አምልኮንና የጉባኤ ጸሎትን የሚመሩ አገልጋዮች ለእግዚአብሔር ክብር፥ ስግደትና አምልኮ ከሚያቀርቡት ጊዜ በላይ ሰይጣንን ለማሰርና ለመሳሰለው የሚወስዱት ጊዜ እየበዛ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከምናነበው እውነት እየራቀ በመሄድ ላይ ስለሆነ ይህን የሚለማመዱና የሚያለማምዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ ያላቸው መሆኑ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው እላለሁ። ጠላትን ለማሠርና ለማወጣት ከተፈለገ በሚገኝበት ስፍራ እንዲወጣ በሥልጣን ማዘዝ ነው፥ በተረፈ ዋና ማሠሪያና ድል ማድረጊያ መሣሪያችን እግዚአብሔርን ማመስገን ነው (መዝ. 149)።

ቀ) የመሪዎች (የዋኖች) ምሳሌአዊ ኑሮ

የቤተ ክርስቲያን ዋናዎች መልካም ምሳሌነት፥ ስጦታዎች በምእመናን ሕይወት በሚገባ እንዲሠራና በአባላት መካከል ሰላምና መግባባት ፍቅር እንዲኖር ለነፍሳትም መጨመር ይረዳልና ይህንን ሽማግሌዎች ተግባራዊ ማድረጋቸው ወሳኝ ነው፤ (1ኛ ጢሞ. 4፡11-12፤

መዝ. 133፡1-3፤ ዮሐ. 13፡34-35፤ የሐዋ. 2፡46-47፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡3)፤ በአገልጋዮች ወይም በምእመናን መካከል አለመግባባት ሲኖርም ከመተማማት ይልቅ በማቴ 18፡15-20 ባለው መሠረት ማስተካከል ተገቢ ነው።

ቡ) <u>የመሪዎች፤ የመጋቢዎችና ወንጌላውያን አባላትን መሀብኘት አስፈላጊነት</u>

ሽማግሌዎች፥ መጋቢዎችና ወንጌላውያን አባላትን መሀብኘትና እንዴት እንዳሉም ማወቅ በመንፈሳዊ ኑሮአቸውም ማበረታትና ለችግራቸው መጸለይና አስፈላጊውን እንዲያገኙ ጥረት ማድረግ ከሐሰት አስተማሪዎችም እነርሱንመጠበቅ በጣም ጠቃሚ ነው (የሐዋ. 15፡36፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡2፤ ዕብ. 10፡24-25፤ ኤር. 22፡11፤ ሕዝ. 34፡1-10)።

11. ቤተ ክርስቲያን ቤተሰቦችን የማጠናከሯ አስፈላጊነት

የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጥንካሬ የሚለካው በዚያች ቤተ ክርስቲያን በሚገኙ ቤተሰቦች ጥንካሬ ነው። ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚመረጡ ሽማግሌዎች ልጆቻቸውን በጭምትነት ሁሉ እየገዙ የራሳቸውን ቤት በመልካም ማስተዳደር ያወቁ መሆን እንዳለባቸው፥ እንዲሁም ዲያቆናት ልጆቻችውንና የራሳቸውን ቤቶች በመልካም እያስተዳደሩ፥ እያንዳንዱ የአንዲት ሚስት ባል ይሁኑ ሲል (1ኛ ጢሞ. 3፡4-5፤ 3፡12) የቤተሰብን መጠናከር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራል።

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ዓለምን በውኃ ሲያጠፋ እርሱን የሚያምነውን ኖህን ከቤተሰቡ ጋር አዳነው። ለአብርሃምም «በዘርህ የምድር አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ» አለው። በዳዊት መዝሙርም ላይ «እግዚአብሔርን የሚፈራ ትእዛዙንም እጅግ የሚወድድ ሰው ምስጉን ነው። ዘሩ በምድር ላይ ኃያል ይሆናል፥ የቅኖች ትውልድ ትባረካለች። ክብርና ባለጠግነት በቤቱ ነው። ጽድቁም ለዘላለም ይኖራል» ይላል (መዝ. 111፡1-3)።

የወህኒ ቤት ጠባቂው ጳውሎስንና ሲላስን ጌቶች ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ባላቸው ጊዜ፥ እነርሱም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ አሉት፤ <u>ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ተጠናክሮ እንዲኖር የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅበታል።</u>

- ወላጆች ልጆቻቸውን ከልጅነታቸው ጀምሮ፥ ለጋብቻ ዕድሜ ሲደርሱ በተቀደሰ ክርስቲያናዊ ጋብቻ እንዲጣመሩ ዓለማውያንን እንዳያገቡ እንዲያስተምሩ፥ ማሰልጠን አለባት።

- የጋብቻ ክቡርነትን ለማሳየት ጋብቻዎች በቤተ ክርስቲያን በቃል ኪዳን እንዲሆኑ መምራትና በዚያ እንዲጋቡ ማበረታታት አለባት።

- የተጋቡትም እስከ ዕለተ ሞታቸው ተዋደውና ተፋቅረው እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲኖሩ መጎብኘት መምከርና በቃሉና በጸሎት፥ በጎብረትም እንዲኖሩ መርዳት ያስፈልጋታል።

- ለተጋቡት የቤተሰብ የቃሉ ንባብ፥ የጸሎትና የአምልኮ ጊዜ እንዲኖራቸው ማበረታታት ይኖርባታል።

- ጋብቻን የሚያጠናክሩ ሴሚናሮችና ወርክሾፖችን እያዘጋጀች የተጋቡ አባሎችን ማሳተፍ ይጠበቅባታል።

- ልጆችም ከተወለዱ በኋላ የነገዋን ቤተ ክርስቲያንን ትውልድ እንዲያገለግሉ ለማሰልጠን ስለ ሕፃናት አስተዳደግ ትምህርትና ለወጣቶችም የሚሆን የቅደመ ጋብቻ ሴሚናር ማዘጋጀትና እነርሱን በሚመለከቱ ችግሮቻቸውና ክርስቲያናዊ ሕይወታቸውን ጠብቀው እንዴት ከተቃራኒ ጾታቸው ጋር አብረው ማገልገል እንደሚችሉ፥ ማሰልጠን ይኖርባታል።

- ይህንንም አገልግሎት ለመስጠት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጋብቻ አማካሪ አገልግሎት ማቋቋም ጠቃሚ ነው። አገልግሎቱንም በዕድሜ ደረጃ በመለየት፥ በጋራና በግል፥ ያላገቡ ወጣቶች፥ እንዲሁም ላገቡ ቤተሰብ በየጋብቻ ዘመናቸው በመከፋፈል በማሰልጠን ሊካሄድ ይችላል።

- የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የጥሩ ትዳር ምሳሌ ቢሆኑ፥ በእነርሱ ምክንያት ምእመናን ጥሩ ቤተሰብ መሥርተው ለመኖር ይጓጓሉና አርአያ መሆናቸው ወሳኝ ነው።

ማጠቃለያ

ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብን በጥሩ ክብካቤ ከያዘች፥ ከጥሩ ቤተሰብ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ልጆች ስለሚወለዱና ስለሚያድጉ፥ ቤተ ክርስቲያንም ተረካቢ ትውልድ እያፈራች ስለምትሄድ፥ ቤተ ክርስቲያንን እንድታድግና እንድታፈራ ከማድረጉም ሌላ አባላት ጠፍተው የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ከመዝጋት ይጠብቃታል።

12. የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን፥ የመሪዎችና የአባላት ሚናዎች

በአሁኑ ወቅት፥ በተቻለ መጠን የራስን ነፃነት ለማወጅ ሁሉም በየበኩሉ ጥረት እያደረገና፥ ሥልጣን ውስጥ እንዲሆን የሚያደርገውን ሆነ፥ የሚመክረውን ሰው አልቀበልም ያለበትና ሥልጣንንም እየተጋፋ ያለበት ጊዜ ነው። እንዲህ ያለው ዓለማዊ አስተሳሰብና ድርጊት ደግሞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልኮ ገብቶ አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናትን ሲያተራምስና ሲያከፋፍል ይታያል። <u>ታዲያ በቤተ ክርስቲያን ላለን ለዚህ መፍትሔው ምንድንነው? መጽሐፍ ቅዱስ ስለሥልጣን ምን ይላል? መልሶችን እንደሚከተለው እናገኝ።</u>

<u>ሥልጣን፡-</u> በጥሬ ቃሉ ሲታይ ማስተዳደርን ሆኒ ማንኛውንም የተሰጠን ኃላፊነት ለማስፈጸም የሚያስችል ሕጋዊ ኃይል ነው። ሥልጣኖችም የተለያዩ ናቸው።

- <u>የእግዚአብሔር ሥልጣን</u> ፡- ዘላለማዊና በፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ ላይ ያለውን ገዥነት ወይምባለሥልጣንነት ያመለክታል። (ዘፍ. 15፡18፤ ኢዮብ 26፡12፤ ኢሳ. 50፡2) እግዚአብሔር በሥልጣኑ፥ ጊዜንና ዘመናትን ወስኗል (የሐዋ. 1፡7) ሁሉን በራሱ ፈቃድ ያደርጋል (ዳን. 4፡34-35) ልክ የሸክላ ሠሪ በሸክላው ላይ ሥልጣን እንዳለው ያህል በፈጠረው ሰው ላይ እግዚአብሔር ሥልጣን አለው (ሮሜ. 9፡20-23) ሥልጣን ሁሉ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው፥ አግዚአብሔር ካልፈቀደ ሰው በራሱ ሥልጣን የለውም (ሮሜ 13፡1) ይቅር ለማለትና ሊያፀድቅ ወይም ሊኮንን ሥልጣን አለው (ሮሜ. 3፡21-26፤ ማር. 2፡5-8፤ ሉቃስ 12፡5) ክርስቶስ ኢየሱስ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቷታል የቤተ ክርስቲያንም ራስ ነው (ኤፌ. 1፡19-23፤ ማቴ. 28፡18)።

<u>መጽሐፍ ቅዱስም</u> ፡- የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ሥልጣን አለው (ኢሳ. 55፡11፤ ማቴ. 24፡35፤ ገላ. 1፡8-9)። ሐዋርያትም የቤተ ክርስቲያንን አባላት ለማዘዝ የቤተ ክርስቲያንንም ትምህርትና ሥርዓት ለመወሰን ሥልጣን ነበራቸው (2ኛ ቆሮ. 10፡8፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡3-5)።

<u>ዛሬም ቤተ ክርስቲያን አባላትን በተመለከተ ለመወሰን መንፈሳዊ ሥልጣን አላት</u>

<u>የምእመናን ጉባኤ ሥልጣን</u>፥ በአዲስ ኪዳን ሁሉም አባላት ካህናት ስለሆኑ የመወሰን ሥልጣን አላቸው (1ኛ ጴጥ. 2፡9፤ የሐዋ. 15፡22) ሽማግሌዎችንና ዲያቆናትን ለመምረጥ ይችላሉ (የሐዋ. 6፡3-6፤ 15፡22፤ 1ኛ ቆሮ. 16፡3)

ራሳቸውን ከሐሰተኛ አስተማሪዎች የመጠበቅ ኃላፊነት አላቸው (2ኛ ዮሐ. 9-10) አቤቱታ ለመቀበል ሥልጣን አላቸው ፤ማቴ. 18፡17)፥ አጥፊ አባላትን የመቅጣት የማስወገድ ሥልጣን አላቸው (ሮሜ. 16፡17-18፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡1-13) የማሰርና የመፍታት ሥልጣን አላቸው (ማቴ.

18፡18፤ ዮሐ. 20፡22-23) ሆኖም ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ከተሰጣት ሥልጣን አልፋ መወሰን አይገባትም።

<u>የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በአባላት ላይ ሥልጣን አላቸው</u> (1ኛ ተሰ. 5፡12-13፤ ዕብ. 13፡17)

ሆኖም መንፈሳዊ ስልጣን እንደ ዓለም ያለ በሌላው ላይ የመሰልጠን ሥልጣን ሳይሆን የፍቅርና የውክልና ሥልጣን ነው (ማቴ. 20፡25-28፤ የሐዋ. 20፡28፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡1-4)፤ ስለሆነም ያለ በቂ ማስረጃ በአንድ ምእመን ላይ እርምጃ መውሰድ ማሰናከያ ሊሆን ስለሚችል እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

አባላትም ቤተ ክርስቲያን በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ የምትወስነውን ሹመትና ሽግግሌዎችንም ማክበር ይጠበቅብናል። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጴጥሮስ በ1ኛ መልእክቱ 5፡5 «ጎበዞች ሆይ ለሽማግሌዎች ተገዙ፥ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ፥ ትህትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፥ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ ለትሁታን ግን ጸጋን ይሰጣል» ያለው እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ በዕብ. 13፡17 ላይ «ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው ይህንኑ በደስታ እንጂ በሀዘን እንዳያደርጉት ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ» ብሎ የሚመክረን፤ ስለሆነም ማናችንም የእግዚአብሔርን ሥርአት ማክበር ሲኖርብን «የነብያት መናፍስት ለነብያት ይገዛሉ፤ እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና፤ በቅዱሳንም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲህ ነው የሚለውን ልብ እንበል፤ እግዚአብሔርም ትእዛዙን እንድንቀበል ጸጋውን ያብዛልን (1ኛ ቆሮ. 14፡32-33)።

ወዳጆቼ ሽማግሌዎች ሆይ! የእናንተ ስልጣን በአደራነት የተሰጠ ስለሆነ በባለ አደራነት መንጋዉን በትህትና አስተዳድሩ። ሌሎች ደግሞ እንዲፈሩ፥ ኃጢአት የሚሠሩትን በሁሉ ፊት ገሥጹአቸው (1ኛ ጢሞ. 5፡20) ያለሥርዓት የሚሄዱትን ገሥጹአቸው፥ ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው፥ ለደካሞች ትጉላቸው፥ ሰውን ሁሉ ታገሱ (1ኛ ተሰ. 5፡14)።

<u>ማጠቃለያ</u> ፡- ሁላችንም በተቀደሰ ሃይማኖታችን ራሳችንን ለማነጽ እየተጋን፥ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል እየጸለይን፥ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት እየተጠባበቅን፥ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችንን እንጠብቅ።አንዳንዶች ተከራካሪዎችን እንወቅስ፥ አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቀን እናድን፤ አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳ እየጠላን፤ በፍርሃት እንማር» «ሳንሰናከል ለሚጠብቀን፥ በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌለን አድርጎ ሊያቆመን ለሚችለው ብቻውን ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን፥ ከዘመን ሁሉ በፊት፥ አሁንም፥ እስከ ዘላለም ድረስ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ግርማ ኃይልም ሥልጣንም ይሁንለት፤ አሜን» (ይሁዳ 20-25)